# Ee


*E,e* (ኢ:)
የእንግሊዝኛ አምስተኛው ፊደል

*each* (ኢ:ች)
እያንዳንዱ
Each child has a pencil.
እያንዳንዱ ልጅ እርሣስ አለው።

*eagle* ('ኢ:ግል)
/ንስር/ ትልቅ ስጋ የሚበላ አሞራ
The eagle caught the snake in its claws.
ንስሩ እባቡን በጥፍሮቹ ያዘው::



*ear* (ኢ.የ)
ጆሮ/ድምፅ የምንሰማበት
የሰውነታችን ክፍል
She has an earring on her ear.
በጆሮዋ ላይ የጆሮ ጌጥ አድርጋለች።



*earring* (ኢ.የ ሪን)
የጆሮ ጌጥ/ሎቲ
Her earing is beautiful.
የጆሮ ጌጥዋ ቆንጆ ነው።



*early* ('ኧ:ሊ)
1. ገና ከመጀመሪያው
The athlete fell early in the race.
ገና ሩጫው ሲጀመር ሯጩ ወደቀ።
2. ከሚጠበቅበት ከጊዜው
ቀድሞ አንድ ድርጊት ሲፈፀም
The rain came early this year.
ዝናቡ በዚህ አመት ከሚጠበቅበት
ጊዜ ቀድሞ መጣ።

*earn* (ኧ:ን)
ተሰርቶ የሚገኝ ገንዘብ
He earns money every week.
እሱ በየሳምንቱ ገንዘብ ያገኛል።

*earth* (ኧ:ስ)
1. ምድር/ የምንኖርባት አለም
How many people live on the earth?
በአለም ላይ ስንት ሰዎች ይኖራሉ?




2. መሬት/አፈር
Plants need good earth to grow in.
እፅዋት ለመብቀል ጥሩ አፈር ይፈልጋሉ።

*earthquake* ('ኧ:ስ ክዌክ)
የመሬት መንቀጥቀጥ
The city is destroyed by the earthquake.
ከተማው በመሬት መንቀጥቀጥ ጠፋ።

*easel* ('ኢ:ዝል)
ስእሊ ስራውን ስቅሉ የሚሠራበት ተንቀሣቃሽ ስእል መስቀያ
They put the picture on the easel.
ስእሉን በስእል መስቀያው ላይ አስቀመጡት።



*east* ('ኢ:ስት)
ምስራቅ/ሀሀይ የምትወጣበት አቅጣጫ
The sun rises in the east.
ፀሀይ በምስራቅ ትወጣለች፡




*Easter* ('ኢ:ስተ)
ፋሲካ/የክርስቶስ ሞቶ መነሣት የሚታሰብበት የክርስትና በአል/
Easter Sunday is a joyful day for Christians.
የፋሲካ እሁድ ለክርስቲያኖች የደስታ ቀን ነው።

*easy* ('ኢ:ዚ)
ቀላል የማያስቸግር ስራ
The work was easy.
ስራው ቀላል ነበር።

*eat* (ኢ:ት)
መብላት/ወደ አፍ ከቶ ማኘክ
My mother told us to eat our potatoes.
እናቴ ድንቾቻችንን እንድንበላ ነገረችን።



*echo* (ኤከው)
/የገደል ማሚቶ/ ገደል ጋ ሆነን ስንጮህ ተመልሶ የሚሠማን ድምፅ/ የሚያስተጋባ ድምፅ
My voice echoed around the cave.
በዋሻ ዙሪያ ድምፄ አስተጋባ።

*edge* (ኤጅ)
1. ዳርቻ/የአንድ ነገር ጫፍ/ጠርዝ/
The boy plays at the edge of the river.
ልጁ በወንዙ ዳርቻ ላይ ይጫወታል።



2. ስለት/ የሚቆርጠው የቢላዋ ክፍል
He cut the bread by the edge of the knife.

ዳቦውን በቢላዋው ስለት ቆረጠው።



*educate* ('ኤጁኬይት)
አስተማረ/አሰለጠነ/አሳወቀ
We go to school to be educated.
ለመማር ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን።

*egg* (ኤግ)
እንቁላል
We eat hens' egg.
የዶሮ እንቁላል እንበላለን።



*eight* (ኤይት)
ስምንት/8/
Eight people got out of the bus.
ስምንት ሰዎች ከአውቶቡስ ወረዱ።

*eighteen* (ኤይ'ቲ:ን)
አስራ ስምንት/18/
My uncle bought eighteen goats yesterday.
አጎቴ ትላንት አስራ ስምንት ፍየሎች ገዛ።

*eighty* ('ኤይቲ)
ሰማንያ/80/
Some elephants are eighty years old.
አንዳንድ ዝሆኖች ሰማንያ አመት ይሆናቸዋል።

*either* ('አይዘ)
1. ከሁለት አንዱ
2. ሁለቱም 3. ከሁለቱም የፈለገውን/የመረጠውን
We will take either the taxi or the bus.
ታክሲ ወይም አውቶብስ እንይዛለን።

*elastic* (ኢ'ላስቲክ)
ተስቦ ሲለቀቅ ወደ ቦታው የሚመለስ/የሚሣብ/የሚለጠጥ
I have got an elastic belt.
የሚሳብ ቀበቶ አለኝ።

*elbow* ('ኤልበው)
ክርን
He put his elbow on the table.
ክርኑን ጠረጴዛው ላይ አስደገፈ።



*elder* ('ኤልደ:)
1. ሽማግሌ/አዛውንት
My father always tells me to respect elders.
አባቴ ሁልጊዜ ሽማግሌዎችን እንዳከብር ይነግረኛል።
2. ታላቅ/ በእድሜ የበለጠ በቤተሰብ ውስጥ
He is my elder brother .
እሱ ታላቅ ወንድሜ ነው።

*electricity* (ኢሌክ'ትሪሰቲ)
የኤሌክትሪክ ሀይል
Electricity is the source of our light .
የመብራታችን ምንጭ የኤሌክትሪክ ሃይል ነው።



*elementary* (ኤሊ'ሜንትሪ)
የመጀመሪያ ደረጃ/ የአንደኛ ደረጃ
This dictionary is for elementary school students.
ይህ መዝገበ - ቃላት ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ነው።

*elephant* ('ኤሊፈንት)
ዝሆን/በዱር ከሚኖሩ እንስሣት ሁሉ ትልቁ እንስሣ/
Elephants have big ears.
ዝሆኖች ትልልቅ ጆሮዎች አሏቸው።



*eleven* (ኢ'ሌቭን) ስ-
አስራአንድ (11)
Eleven comes after ten.
አስራ አንድ ከአስር ቀጥሎ ይመጣል።

*empty* (ኤምፕቲ)
ባዶ/ውስጡ ምንም የሌለው/
He moved into an empty house.
እሱ ወደ ባዶ ቤት ገባ።

*encyclopaedia* (ኢንሳይክለ'ፒ፡ዲየ)
አውደ ጥበብ/ስለማንኛውም ነገር መረጃ የሚሰጥ መፅሀፍ
I have got this story from encyclopedia.
ይህንን ታሪክ ያገኘሁት ከአውደ ጥበብ ነው።

*end* (ኤንድ)
መጨረሻ/ የአንድ ነገር መጨረሻ ማብቂያ
The teacher didn't tell us the end of the story.
መምህሩ የታሪኩን መጨረሻ አልነገሩንም።

*enemy* ('ኤነሚ)
ጠላት/የማይዋደዱ ሰዎች
The two countries have been enemies for years.
ሁለቱ ሃገሮች ለአመታት ጠላት ነበሩ።

*engine* ('ኤንጂን)
ሞተር (መኪና፣ ባቡር፣ አይሮፕላን ሁሉ የሚያንቀሣቅስ አካል
It needs two engines to pull the heavy train.
ከባዱን ባቡር ለመጎተት ሁለት ሞተር ያስፈልጋል።




*enjoy* (ኢን'ጆይ)
**መደሰት**
I enjoy singing in the church.
**ቤተክርስቲያን ውስጥ መዘመር ደስ ይለኛል።**

*English* ('ኢንግሊሽ)
1. **የእንግሊዝ የሆነ ነገር ሁሉ**
This is an English man.
**ይህ እንግሊዛዊ ሰው ነው።**
2. **የእንግሊዝኛ ቋንቋ**
English is my second language.
**እንግሊዝኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋዬ ነው።**

*enough* (እ'ነፍ)
**በበቂ መጠን/የሚበቃውን ያህል**
Have we got enough food to eat?
**የምንበላው በቂ ምግብ አለን?**

*entrance* ('ኤንትረንስ)
**መግቢያ በር**
The entrance to the house has an iron gate.
**የቤቱ መግቢያ የብረት በር አለው።**



*envelope* (ኢን'ቬለፕ)
**ፖስታ/የደብዳቤ መያዣ ወረቀት/**
She wrote the address on the envelope.
**ፖስታው ላይ አድራሻ ፃፈች።**

*escape* (ኢ'ስኬይፕ)
**ማምለጥ/ከተያዙበት ከታሰሩበት ቦታ ነፃ መሆን/**
The lion escaped from its cage.
**አንበሳው ከብረት ቤቱ አመለጠ።**

*evening* ('ኢ፡ቭኒን)
**ምሽት/መሸትሸት ሲል በጣም ሳይጨልም**
Children ran back to their homes in the evening.
**ሲመሻሽ ልጆች ወደ ቤታቸው ይሮጣሉ።**



*ever* ('ኤቨ)
**መቼም/ምንጊዜም/ሁልጊዜ/ በማንኛውም ጊዜ**

I will not see my dead dog ever again.
የሞተውን ውሻዬን መቼም ቢሆን አላገኘውም።

*every* ('ኤቭሪ)
እያንዳንዱ ሁሉም
The shop is open everyday.
ሱቁ በሁሉም ቀናት ክፍት ነው።

*everybody* ('ኤቭሪቦዲ)
በሙሉ/ሁሉም ሰው)
My mother invited everybody in my village to the wedding.
እናቴ የመንደራችንን ሰው ሁሉ ለሠርጉ ጋበዘች።

*examination* (ኢግዛሚ'ኔይሽን)
1. ፈተና
Abebe passed his English examination.
አበበ የእንግሊዝኛ ፈተናውን አለፈ።
2. ምርመራ
The doctor made a careful examination of my sister's eye.
ሃኪሙ የእህቴን አይን በጥንቃቄ መረመረ።

*example* (ኢግ'ዛ:ምፐል)
ምሳሌ/ አንድን ነገር ለማረጋገጥ የሚቀርብ ማስረጃ
Write an example for each exercise.
ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ጻፍ።

*excuse* (ኢክ'ስክዩ:ዝ)
ይቅርታ ማድረግ
Excuse me can you tell me your name?
ይቅርታ አድርግልኝና ስምህን ልትነግረኝ ትችላለህ?

*exercise* ('ኤክሰሳይዝ)
1. ሰውነትን የሚያጠነክር እንቅስቃሴ
Sport is a good exercise for your health.
የስፖርት እንቅስቃሴ ለጤንነት ጥሩ ነው።



2. መልመጃ
The teacher gave the class an exercise to do.
መምህሩ ለተማሪዎቹ የሚሠሩት መልመጃ ሰጠ።

*explain* (ኢክ'ስፕሌይን)
የአንድን ነገር ትርጉም ማብራራት/ መግለፅ
The farmer explained how to milk the cow.
ገበሬው ላም እንዴት እንደምትታለብ አብራራ።

*explode* (ኢክ'ስፕለውድ)
መፈንዳት/አንድ ሙሉ የነበረ ነገር ከፍተኛ ድምፅ አሰምቶ ወደ ትንንሽ ነገሮች ሲቀየር/ሲፈራርስ
The petrol tank caught fire and exploded.

የቤንዚን መያዣው በእሳት ተቀጣጥሎ ፈነዳ።



*explore* (ኢክ'ስፕሎ፡)
በየአገሩ እየዞሩ አዳዲስ ነገሮችን ማየት መመርመር
The boy had great fun exploring the caves.
ልጁ ዋሻውን በማየቱ በጣም ተደስቷል።

*expression* (ኢክስ'ፕሬሽን)
1. በሰው ፊት ላይ የሚታይ ስሜት
She had a sad expression.
እሷ የሀዘን ስሜት ይነበብባታል።
2. አባባል /አንድ ነገር ለመግለፅ የሚጠቀሙበት/ አገላለፅ
"Shut up" is a hard expression.
"ዝጋ" ከበድ ያለ አገላለፅ ነው።

*eye* (አይ)
አይን/የምናይበት የሰውነት አካል
She has beautiful eyes.
የሚያማምሩ አይኖች አሏት ።



*eyeglass* (አይ ግላስ)
የአይን መነፅር
Look at my eyeglasses they are beautiful.
መነፅሬን ተመልከት ያምራል።



*Ff* (ኤፍ)
የእንግሊዝኛ ስድስተኛ ፊደል

(ፌይስ)
1. ፊት/አይን፣ አፍንጫ፣ አፍ ያለበት የሰውነት ክፍል/
The dog has a furry face.
ውሻው በፀጉር የተሸፈነ ፊት አለው።



2. ከአንድ ነገር ጋር ፊት ለፊት የተያየ ትይዩ
Our house faces the school.
ቤታችን ከትምህርት ቤቱ ትይዩ ነው።



*factory* (' ፋክትሪ)
ፋብሪካ/የተለያዩ ነገሮች ለምሳሌ ልብስ፣ ጫማ፣ መኪና የሚሠሩበት የሚመረቱበት ቦታ/
My uncle works in a factory that makes cars.
አጎቴ የመኪና ፋብሪካ ውስጥ ይሰራል።

*fade* (ፌይድ)
አንድ ነገር ቀለሙ እየለቀቀ/ እየፈዘዘ ሲሄድ። ለድምፅም እየደከመ/ እየቀነሰ ሲሄድ።
The sound of the cars faded into the distance.
የመኪናዎቹ ድምፅ እየራቁ ሲሄዱ ቀነሰ።

*fail* (ፌይል)
ፈተና መውደቅ/ሳያልፉ መቅረት/ ያልተሳካ
He failed to pass his history exam.
እሱ የታሪክ ፈተናን ሳያልፍ ቀረ።

*fair* (ፌየ)
1. ነጣ ያለ በጣም ያልጠቆረ/ለፀጉር ለቆዳ/
I have fair hair. My brother has black hair.
እኔ ነጣ ያለ ፀጉር አለኝ። ወንድሜ ጥቁር ፀጉር አለው።
2. አንዱ ከአንዱ ያልተበላለጠ
The teacher distributed the biscuits fairly.
አስተማሪዋ ብስኩቶቹን ለማንም ሳያዳሉ እኩል አከፋፈሉ።
3. በጣም ጥሩ የማይባል/ ደህና
I did fairly well in my exams.
ፈተናዬን ደህና ሰርቻለሁ።

*fall* (ፎል)
ከአንድ ነገር ላይ ወደ መሬት መውደቅ
He fell off the horse and hurt his leg.

ከፈረስ ወድቆ እግሩ ተጎዳ።

*family* ('ፋሚሊ)
ቤተሰብ/ እናት፣ አባት፣ ልጆች
በአንድነት/
My mother ,father and brothers
are my family.
እናቴ፣ አባቴና ወንድሞቼ የኔ
ቤተሰቦች ናቸው።



*famine* ('ፋሚን)
ድርቅ/ የሚበላ ነገር የሌለበት ጊዜ/
እህል አልበቅል ሲል
Famine makes people strave.
ድርቅ ሕዝብን ረሀብተኛ ያደርጋል።

*famous* (ፌይመስ)
የታወቀ/ዝነኛ ብዙ ሰዎች የሚያውቁት/
Everyone wanted to see the
famous singer.
ሁሉም ሰው ታዋቂውን ዘፋኝ
ለማየት ፈለገ።

*far* (ፋ:)
ሩቅ/አንዱ ከአንዱ በጣም የተራራቀ/
Africa is far from America.
አፍሪካ ከአሜሪካ ትርቃለች።

*fare* (ፌየ:)
ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ለመሄድ
ለታክሲ ወይም ለአውቶቡስ የሚከፈል
ዋጋ
Fanaye paid the bus fare into
town.
ፋናዬ ከተማ ለመሄድ የአውቶቡስ
ዋጋ ከፈለች።

*farm* (ፋ:ም)
እርሻ/መሬት ተቆፍሮ የሚተከልበት፣
ከብቶችየሚረቡበት ቦታ/
The farmer keeps cattle and goats
on his farm.
ገበሬው በእርሻው ውስጥ ከብቶችና
ፍየሎች አሉት።

*fast* (ፋ:ስት)
በጣም በፍጥነት/ፈጣን



He drives his car too fast.
መኪናውን በጣም በፍጥነት ይነዳል።

*fasten* ('ፋ:ስን)
መቆለፍ/በርን(መዝጊያን)
Please fasten the gate to keep the
cows in.
ላሞቹ እንዳይወጡ እባክህ በሩን
ቆልፈው።

*fat* (ፋት)
1. ወፍራም
My cat eats too much. She is very
fat.
ድመቴ ብዙ ትበላለች። በጣም
ወፍራም ነች።



2. ጮማ/ሰውነት ውስጥ የሚገኝ ነጭ ስጋ/
Please cut the fat off the meat before cooking it.
ስጋውን ከማብሰልህ በፊት ጮማውን ቁረጠው።

*r* ('ፋ:ዘ)
አባት/ ልጆች ያሉት ወንድ ሰው
My father is a teacher.
አባቴ አስተማሪ ነው።



(ፎ:ልት)
አንድ ነገር እንዳይሰራ የሚያደርግ ችግር ወይም ብልሽት
There is a fault in the cooker. It is not working.
የምግብ ማብሰያው አይሰራም። ብልሽት አለው።

*urite* ('ፌይቨሪት)
የሚመርጡት/ከብዙ ነገሮች አንደኛ የሚወዱት/
Red is my favourite colour.
ቀይ ከሁሉም ቀለማት የምወደው ቀለም ነው።

*fear* (ፊየ)
ፍርሃት/አስደንጋጭ ነገር ሲያጋጥመን የሚሠማን ስሜት/
They began to shake with fear.
በፍርሀት መንቀጥቀጥ ጀመሩ።

*feather* ('ፌዘ)
ላባ/የዶሮ ወይም የወፎች አካል ሽፋን
Birds are covered with feathers.
ወፎች በላባ የተሸፈኑ ናቸው።



*February* ('ፌብሩወሪ)
የካቲት/በጎርጎርሣውያን የአመቱ 2ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 6ኛ ወር/
My sister's birthday is in February.
የእህቴ ልደት በየካቲት ነው።

*feeble* ('ፊ:ብል)
ደካማ/ አቅመ ቢስ
The old lady felt very feeble after her illness.
አሮጊቷ ከታመመው በኋላ ድካም ተሰማቸው።

*feed* (ፊ:ድ)
እንጀራ፣ ዳቦ/ የሚበላ ነገር ማብላት/ መመገብ
I will feed the dog tonight.
ውሻውን ዛሬ ማታ አበላዋለሁ።

*female* ('ፊ:ሜይል)
እንስት ያታ/ሴት/
ሴት እንስሣት በሙሉ /የእህት፣ የእናት፣ ያታ

My mother, my sister, my aunt and daughter all are females.
እናቴ፣ እህቴ፣ አክስቴና ሴት ልጄ ሁሉም ሴቶች ናቸው።



*fence* (ፌንስ)
አጥር/እንጨት ወይም ሽቦ አንድ ቦታ ዙሪያውን የሚከበብበት/
We have a wooden fence around our house.
በቤታችን ዙሪያ የእንጨት አጥር አለን።



*ferry* ('ፌሪ)
እቃን ከአንድ ቦታ ወደሌላ የሚያመላልስ በባህር ላይ የሚንሳፈፍ የእቃ ጀልባ
The ferry carried the lorries across the river.
የማመላለሻ ጀልባው የጭነት መኪናዎቹን ተሸክሞ ወንዙን አሻገራቸው።

*fetch* (ፌች)
አንድን ነገር ሄዶ ማምጣት በተለይ ውሃ ለመቅዳት
My mother walks a long distance to fetch water.
እናቴ ውሀ ለመቅዳት ረጅም መንገድ በእግሯ ትጓዛለች።

*few* (ፍዩ፡)
በጣም ትንሽ/ጥቂት/ከባዶ የማይሻል
There are a few seats left on the bus.
አውቶቡሱ ውስጥ ጥቂት ባዶ መቀመጫዎች አሉ።

*field* (ፊ፡ልድ)
ማሳ/ሜዳ/ እህል የሚበቅልበት የሚታጨድበት/
We have a good field of corn this year.
በዚህ አመት ጥሩ የበቆሎ ማሳ አለን።



*fierce* (ፊየስ)
የተቆጣ/አደገኛ/ በጣም የሚፈራ/ ሃይለኛ
There is a fierce dog in there.
እዚያ ውስጥ ሃይለኛ ውሻ አለ።

*fifteen* (ፊፍ'ቲ፡ን)
አስራ አምስት/15/
Alem is fifteen years old today.
አለም ዛሬ አስራ አምስት አመት ሆናት።

*fifty* ('ፊፍቲ)
ሀምሳ /50/
It is fifty kilometres to go to Akaki and come back.
ከዚህ እስከ አቃቂ ደርሶ መልስ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ነው።

*fight* (ፋይት)
ጥል/ በሁለት ወይም ከዛ በላይ ሰዎች ወይም አገሮች መሃከል የሚደረግ ጦርነት/ረብሻ/
My brother always fights over the biggest piece of cake.
ወንድሜ ሁልጊዜ ትልቁን ኬክ ለመውሰድ ይጣላል።

*figure* ('ፊገ)
1. አንድን ነገር ለመቁጠር የምንጠቀምበት አሀዝ/ቁጥር
1,2,3 are all figures.
1,2,3 አሀዞች ናቸው።
2. የሰው ተክለ ሰውነት/መላ ሰውነት እጅ፣ እግር፣ ጭንቅላት
The figure of the man disappeared into the night.
የሰውየው ተክለ ሰውነት በጨለማው ውስጥ ጠፋ።

*fill* (ፊል)
አንድን ነገር በእቃ መሙላት
They filled the tank of the car with petrol.
የመኪናውን ነዳጅ መያዣ በቤንዚን ሞሉት።

*fin* (ፊን)
የአሣ ክንፍ/ለመዋኘት የሚረዳ የአሳ አካል
The fish uses its fins to turn in the water.
አሳው በውሀ ውስጥ ለመዘዋወር ክንፉን ይጠቀማል።



*find* (ፋይንድ)
አገኘ/የጠፋን ነገር/
Can you find my coat?
ኮቴን ልታገኘው ትችላለህ

*finger* ('ፊንገር)
ጣት
He wore a gold ring on his finger.
ጣቱ ላይ የወርቅ ቀለበት አድርጓል።



*finish* ('ፊኒሽ)
መጨረስ/የጀመሩትን ነገር መፈጸም/
You can go home when you have finished your work.
ስራህን ስትጨርስ ወደቤትህ መሄድ ትችላለህ።

*fire* ('ፋየር)
እሳት


Brook lit the fire to cook the meat.
ብሩክ ምግቡን ለማብሠል እሣት አቀጣጠለ።



*firm* (ፈ:ም)
1. የንግድ ድርጅት
He works in a firm.
እሱ የንግድ ድርጅት ውስጥ ይሠራል።
2. አንድን ነገር ጠበቅ አድርጎ ማሠር ወይም መያዝ
We fixed the shelf firmly to the wall.
የመፅሀፍ መደርደሪያውን ግድግዳው ላይ አጥብቀን አሠርነው።

*first* (ፈ:ስት)
የመጀመሪያ ከሁሉ በፊት
She sat in the first row so that she could see better.
እሷ የመጀመሪያ መደዳ ስለተቀመጠች በደንብ መመልከት ትችላለች።

*fish* (ፊሽ)
አሣ/በባሕር ውስጥ የሚኖር እንስሣ/
The lake is full of fish.
ሀይቁ በአሣ የተሞላ ነው።
2. ከወንዝ/ከባህር ውስጥ አሳን መያዝ
My father is going to fish in the lake.
አባቴ ከሀይቁ አሣ ለማጥመድ ይሄዳል።



*fisherman* (ፊሸመን)
አሳ አጥማጅ/ ከባህር ወይም ከወንዝ አሳ የሚይዝ ሰው
My uncle is a fisherman.
አጎቴ አሳ አጥማጅ ነው።



*fist* (ፊስት)
ቡጢ/ጡንቻ/እጅን ጨብጦ መምታት/
The two boys were having a fist fight.
ሁለቱ ልጆች ቡጢ ገጥመው ነበር።



*fit* (ፊት)
የልብስ/የጫማ ልክ መሆን
The dress did not fit me, it was too small.
ቀሚሱ ትንሽ ስለነበር አልተስማማኝም/ አልበቃኝም።

*five* (ፋይቭ)
አምስት /5/
She bought five books.

እሷ አምስት መጻህፍት ገዛች።

*fix* (ፊክስ)
አንድን ነገር አንድ ነገር ላይ መግጠም
The picture is fixed firmly to the wall.
ስዕሉ ግድግዳው ላይ በደንብ ተገጥሟል።
2. መወሰን/ለምሣሌ የቀጠሮ ቀንን
We fixed a day next week to go to the shop.
በሚቀጥለው ሳምንት ወደ ሱቅ ለመሄድ ቀን ወሰንን።

*flag* (ፍላግ)
ባንዲራ/የአንድ አገር ሰንደቅ አላማ/
Every country has its flag.
ማንኛውም ሀገር የራሱ ባንዲራ አለው።



*flame* (ፍሌይም)
ነበልባል/እሳት ሲነድ የሚወጣው ቀይ ነገር/
The flames are jumping from the fire.
ነበልባሉ ከእሣቱ ውስጥ ወደላይ እየዘለለ ነው።



*flamingo* (ፍለ'ሚንጐ)
ቆልማሚት ወፍ (ውሀ አካባቢ የምትገኝ)
The flamingo is like a pink cloud into the sky.
ቆልማሚት ወፍ እንደ ሀምራዊ ደመና ወደሰማይ ብቅ ይላል።




*flap* (ፍለፕ)
መውለብለብ/ወደዚያና ወደዚህ ማለት/
The washing is flapping in the wind.
የታጠበው ልብስ በንፋሱ ይወዛወዛል።

*flash* (ፍላሽ)
ብልጭታ/ማብለጭለጭ/ለአጭር ጊዜ ታይቶ የሚጠፋ ብርሀን/
A flash of light can be seen in the dark sky.
የብርሀን ብልጭታ በጠቆረው ሰማይ ላይ ሊታይ ይችላል።

*flat* (ፍላት)
ጠፍጣፋ ዝርግ ወይም ለጥ ያለ/ክብ ያልሆነ/
The men tried to make the road flat.
ሰዎቹ መንገዱን ለጥ ያለ ለማድረግ ሞከሩ።


*flight* (ፍላይት)
መብረር/በአየር ላይ ከአንድ ቦታ ተነ ስቶ መሄድ/
When the gun went off the birds took flight.
ጠመንጃው ሲተኮስ ወፎቹ በረሩ።

*float* (ፍለውት)
በአየር ወይም በውሃ ላይ መንሳፈፍ
The balloon floated up to the sky.
ፊኛው ወደ ሰማይ ውስጥ ተንሳፈፈ።




*flock* (ፍሎክ)
መንጋ/በአንድነት የሚኖሩ ለምሳሌ በግ፣ ፍየል፣ ሰው/
The flock of sheep has eaten all the grass.
የበግ መንጋው ሁሉንም ሳር በላው።

*flood* (ፍለድ)
ጎርፍ/በሃይል የሚጎነዝ ውሃ/ከወንዝ በቦይ ወጥቶ የፈሰሰ ውሃ/ የሚያጥለቀልቅ/
The river has flooded the field.
ወንዙ ሜዳውን አጥለቀለቀው።



*floor* (ፍሎ:)
ወለል/የአንድ ነገር ለምሳሌ የመሬት የባህር ዝቅተኛው ፣የስረኛው ክፍል/
The lady bought a new carpet on her floor.
ሴትየዋ ለወለሏ አዲስ ምንጣፍ ገዛች።



*flour* (ፍላወ/ር)
ዱቄት/የተፈጨ ነገር በተለይ የስንዴ የጤፍ/
My mother bought 5 Kg of flour to make bread.
እናቴ ለዳቦ መጋገሪያ አምስት ኪሎ ዱቄት ገዛች።

*flow* (ፍለው)
ከአንድ ነገር ወይም ቦታ ወደሌላ መፍሰስ
The river flows into the sea.
ወንዙ ወደ ባህሩ ይፈሳል።

*flower* (ፍላወ/ር)
አበባ/ዛፎች ላይ የሚበቅል የተለያዩ ቀለማት ያለው ለአይን የሚማርኩ ውብ ቅጠሎች/
The flowers in the vase are pretty.
የአበባ ማስቀመጫው ውስጥ ያሉት አበቦች ያምራሉ።




*fly* (ፍላይ)
1. ዝንብ/ በቆሻሻ ቦታዎች የምትገኝ ነፍሳት
He closed the window to keep the flies out.
ዝንቦቹ እንዳይገቡ መስኮቱን ዘጋው።



2. ሄደ/ተጓዘ በአይሮፕላን
I am going to fly to London next week.
በሚቀጥለው ሣምንት ወደ ለንደን እበራለሁ።



*fog* (ፎግ)
ጉም/በክረምት ጊዜ አየሩን የሚሸፍን ነጭ እርጥብ አየር/ጭጋግ/
You can't see the trees because of the fog.
በጭጋጉ ምክንያት ዛፎቹን ማየት አትችልም።



*fold* (ፎውልድ)
ማጠፍ/መጠኑን ለመቀነስ ወይም ለማስቀመጥ
I folded the letter to put it in the envelope.
ፖስታ ውስጥ ለመክተት ደብዳቤውን አጠፍኩት።

*follow* (ፎለው)
መከተል/አንድ ነገር ከፊት እያዩ ከኋላ ከኋላ መጓዝ/
The cows followed the old man home.
ላሞቹ ሽማግሌውን ተከትለው ወደ ቤት ሄዱ።

*food* (ፉ:ድ)
ምግብ/የሚበላ ነገር/
I hope we have enough food for the party.
ለድግሱ በቂ ምግብ እንዳለን ተስፋ አደርጋለሁ።



*fool* (ፉ:ል)
ሞኝ/ ጅል ሰው/ በቀላሉ ሰው ሁሉ የሚያታልለው/መስራት የማይገባውን የሚሰራ/
Only a fool would climb that high hill.
ያንን ዳገት ሞኝ ብቻ ነው የሚወጣው።

*foot* (ፉት)
እግር/ከቁርጭምጭሚታችን በታች ያለው መሬት የምንረግጥበት የሰውነት


ክፍል
The broken bottle cut her foot.
የተሰበረው ጠርሙስ እግሯን ቆረጣት።



*football* ('ፉትቦ:ል)
እግር ኳስ/ኳስን በእግር እየተቀባበሉ መጫወት/
My brother is in the school football team.
ወንድሜ የትምህርት ቤት የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋች ነው።



*forehead* ('ፎ:ሄድ)
ግንባር/ከአይናችን በላይ ከፀጉራችን ስር ያለው የፊታችን ክፍል/
He brushed his hair back from his forehead.
ፀጉሩን ከግንባሩ ላይ ወደኋላ አበጠረው።



*forest* ('ፎረስት)
ጫካ/ብዙ ዛፎች በአንድነት የበቀሉበት ቦታ/
Many trees in the forest were cut down for firewood.
በጫካ ውስጥ የሚገኙት ብዙ ዛፎች ለማገዶነት ተቆርጠዋል።

*forget* (ፈጌት)
መርሳት/ረሳ/ዘነጋ (ስራን/ሃሳብን)
I forgot to brush my teeth.
ጥርሴን መቦረሽ ረሳሁት።

*forgive* (ፈ'ጊቭ)
ለጥፋት ይቅርታ ማድረግ
Please forgive me for breaking the vase.
የአበባ ማስቀመጫውን በመስበሬ አባክሽ ይቅርታ አድርጊልኝ።

*fork* (ፎ:ክ)
ሹካ
Fork is very useful to eat pasta.
ሹካ ፓስታን ለመብላት በጣም ጠቃሚ ነው።


*form* (ፎ:ም)
ቅጽ/ስለ አንድ ነገር የሚሞላ የተዘጋጀ ወረቀት ለምሳሌ ትምህርት ቤት መመዝገቢያ
We have to fill in the doctor's form.
የሃኪሙን ቅጽ መሙላት አለብን።

*fortnight* ('ፎ:ትናይት)
አስራ አራት ቀን/ሁለት ሳምንት
We are going on holiday for a fortnight.
ለሁለት ሳምንት ለእረፍት እንሄዳለን።

*forty* ('ፎ፡ቲ)
**አርባ/40**
There were forty children in our class.
**በክፍላችን ውስጥ አርባ ልጆች ነበሩ።**

*forward* ('ፎ፡ወድ)
**ወደፊት መጓዝ**
The car moved forward slowly.
**መኪናው በዝግታ ወደፊት ተጓዘ።**

*fountain* ('ፋውንተን)
**ፏፏቴ/ሰው ሰራሽ ውሀ ወደላይ ወጥቶ ቁልቁል ሲመለስ/**
There was a fountain in front of our house.
**ከቤታችን ፊት ለፊት ፏፏቴ ነበር።**



*four* (ፎ፡)
**አራት/4/**
A chair has four legs.
**ወንበር አራት እግር አለው።**

*fourteen* (ፎ፡'ቲ፡ን)
**አስራ አራት /14/**
There are fourteen days in a fortnight.
**በሁለት ሳምንት ውስጥ አስራአራት ቀናት አሉ።**

*fowl* (ፋውል)
**ለምግብነት የሚያገለግሉ የወፍ ዘሮች**
Chickens are fowls.
**ዶሮዎች የሚበሉ የወፍ ዝርያዎች ናቸው።**




(ፎክስ)
**ቀበሮ/በጫካ የምትኖር ውሻ የምትመስል አውሬ**
Foxes live in forests.
**ቀበሮዎች በጫካ ውስጥ ይኖራሉ።**



*fracture* (ፍራክቸ)
**ስብራት/የአጥንት መሰንጠቅ/መሰበር**
He failed and fractured his arm.
**ወድቆ የክንዱ አጥንት ተሰበረ።**

*frame* (ፍሬይም)
**ፍሬም/መቃን/ ፎቶግራፍ ግድግዳ ላይ ሲሰቀል የሚቀመጥበት ከእንጨት ወይም ከላስቲክ የተሠራ ክፈፍ**
That picture needs a new frame.
**ያ ስዕል አዲስ ክፈፍ ያስፈልገዋል።**



*free* (ፍሪ)
1. ምንም ክልከላ የሌለበት እንደፈለገ የሚያደርግ/ነፃ
Birds should not be kept in cages. They should be free.
ወፎች የብረት ጎጆ ውስጥ መቀመጥ የለባቸውም ነፃ መለቀቅ አለባቸው።
2. ገንዘብ ያልተከፈለበት ነገር ነፃ
If you buy six litres of petrol you get free oil.
ስድስት ሊትር ነዳጅ ከገዛህ ነፃ ዘይት ታገኛለህ።

*fresh* (ፍሬሽ)
ትኩስ /ብዙ ያልቆየ ነገር/
We are having fresh fish for dinner.
ለእራት ትኩስ አሳ እንበላለን።

*Friday* ('ፍራዴይ)
አርብ/የሳምንቱ 6ኛ ቀን/
I go to school from Monday to Friday.
ከሰኞ እስከ አርብ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ።

*friend* (ፍሬንድ)
ወዳጅ/ጓደኛ/ ብዙ ጊዜ አብሮ የሚማር፣ የሚጫወት ልጅ
He is my best friend.
እሱ የልብ ጓደኛዬ ነው።

*fright* (ፍራይት)
መፍራት/ መደንገጥ
The snake gave the little girl a fright.
እባቡ ትንሿን ልጅ አስደነገጣት።

*frog* (ፍሮግ)
እንቁራሪት/ውሃ አካባቢ የምትኖር አይኑ ትልልቅ የምትዘልና በሃይለኛ ድምፅ የምትጮህ
Frogs love jumping.
እንቁራሪቶች መዝለል ይወዳሉ።



*from* (ፍሮም)
ከ/የምትለዋን ፊደል ይተካል ቤት-ከቤት ስራ-ከስራ
He flew from Diredawa to Addis Ababa.
ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በረረ።

*front* (ፍሬንት)
ፊት ለፊት/የአንድ ነገር የፊተኛው ክፍል
He saw a picture on the front page of the book.
እሱ በመፅሐፉ ፊት ለፊት ባለው ገጽ ላይ ስእል ተመለከተ።

*frontier* ('ፍሬንቲየ)
የአገር ወሰን/ሁለት ነገሮችን የሚለይ ነገር/
The river is the frontier between the two countries.
ወንዙ በሁለቱ አገሮች መካከል ወሰን ነው።

*frown* (ፍራውን)
መቆጣት/መናደድ
The teacher frowned at the

naughty boy.
አስተማሪው በረባሹ ልጅ ተቆጣ።

*fruit* (ፍሩ፡ት)
ፍራፍሬ /በእሳት ሳይበስሉ የሚበሉ ጣፋጭ ፍራፍሬዎች እንደሙዝ፣ ብርቱካን/
Lemons, bananas and oranges are types of fruits.
ሎሚ. ሙዝና ብርቱካን ያፍራፍሬ አይነቶች ናቸው።



(ፍራይ)
መጥበስ/እሳት ላይ በዘይት ብቻ ማብሰል/
Chips are fried slices of potato.
ችፕስ በስሱ ተቆርጠው የተጠበሱ ድንቾች ናቸው።

*full* (ፉል)
ሙሉ/ሙሉ ለሙሉ
The moon is full.
ጨረቃዋ ሙሉ ናት።




*fun* (ፈን)
ደስታ/ጨዋታ /ቀልድ
We had great fun at the party.
በድግሱ ላይ በጣም ተደስተናል።

*fur* (ፈ፡)
ፀጉር/በእንስሳት/በሰውነት አካል ላይ የሚበቅል/
Leopards have spotted fur.
አነሮች ዝንጉርጉር ፀጉር አላቸው።



(ፈ፡ኒቸ)
እቤት ውስጥ የምንገለገልባቸው እቃዎች. ለምሳሌ ወንበር ጠረጴዛ የመሳሰሉት
My mother bought some new furniture for the house.
እናቴ ለቤቱ አዲስ እቃ ገዛች።



*G, g* (ጂ:)
በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሰባተኛው ፊደል

*gain* (ጌይን)
አገኘ/አንድን ነገር ማግኘት/
He has gained good results in his school work.
በትምህርቱ ጥሩ ውጤት አምጥቷል።

*gale* (ጌይል)
አውሎ ነፋስ/ሀይለኛ ነፋስ/ጥፋት የሚያደርስ/
The trees blew down in the gale.
በአውሎ ንፋሱ ዛፎቹ ወደቁ።

*gallop* (ጋለፕ)
ሽምጥ መጋለብ/ለፈረስ/በሀይል መሮጥ/
The horse galloped across the field.
ፈረሱ ሜዳውን አቋርጦ ሽምጥ ጋለበ።



*game* (ጌይም)
ጨዋታ/አጨዋወት/ግጥሚያ
/እራስን ለማዝናናት/ለማስደሠት የሚደረግ እንቅስቃሴ/ስፖርት
Football is a game.
እግር ኳስ ጨዋታ ነው።

(ጋንግ)
የስራ ቡድን/ (የቀን ሰራተኞች) አብረው የሚሠሩ ሰዎች በቀን ክፍያ
The gang of workmen mended the road.
የቀን ሠራተኞች ቡድን መንገዱን ጠገነው።



(ጋፕ)
ቀዳዳ/በነገሮች መሃል ያለ ክፍተት/
The horse escaped through the gap in the fence.
ፈረሱ በአጥሩ መካከል ባለው ቀዳዳ አመለጠ።

(ጋራዥ)
ጋራዥ/መኪናዎች የሚታደሱበት ቦታ/
I put my car in the garage.
መኪናዬን ጋራዥ አስገባሁት።



*garden* (ጋ:ድን)
የአትክልት ቦታ/አበቦች፣ የጓሮ አትክልቶች የሚተከሉበት የሚያድጉበት ቦታ/

I picked a basket of beans from the garden.
ቅርጫት ሙሉ ባቄላ ከአትክልት ቦታው ለቀምኩ።



(ጋስ)
ጋዝ/በከብራት ሲለኮስ እሣት የሚፈጥር አየር/ ለምግብ ማብሠያ የሚያገለግል
We cook our food on the gas cooker.
ምግባችንን በጋዝ ምድጃው እናበስላለን።

(ጋ፡ስፕ)
ትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ ማለት/ ቶሎ ቶሎ መተንፈስ
The boy gasped for breath after swimming under water.
በውሀ ውስጥ ለውስጥ ከዋኘ በኋላ ልጁ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ።

(ጌይት)
በር/የውጭ በራፍ/ለመግቢያና ለመውጪያ የሚያገለግል የአጥር ጊቢ በር
Shut the gate or the dog will get out.
የአጥሩን በር ዝጋው አለበለዚያ ውሻው ይወጣል።



*gather* ('ጋዘ)
መሰብሰብ/በአንድ ላይ መቀመጥ
The people gathered in the church.
ሰዎቹ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ተሰበሰቡ።

*gear* (ጊየ/ር)
ማርሽ
He put the car in a low gear to get it up the hill.
ዳገቱን ለመውጣት አንደኛ ማርሽ አስገባ።

*gentle* ('ጄንትል)
በጣም ረጋ ያለ/ቀስ ብሎ
The cat lifted the kitten gently in its mouth.
ድመቷ ልጆቿን ረጋ ብላ በአፏ አነሣቻቸው።

*geography* (ጂእግረፊ)
ስነ መልከአ ምድር/ጂኦግራፊ/ ስለወንዝ ተራራ አገር የሚያስረዳ የትምህርት አይነት
We were learning about Australia in our Geography class Yesterday.
በትናንትናው የስነመልከአምድር ትምህርታችን ስለ አውስትራሊያ

ስንማር ነበር።


*get* (ጌት)
ማምጣት/አንድን ነገር ካለበት ቦታ ማግኘት
Can you get me the newspaper from the table?
ጋዜጣውን ከጠረጴዛው ላይ ልታመጣልኝ ትችላለህ?

*giant* (ጃይየንት)
ግዙፉ ሰው/የሚያስፈራና ትልቅ ፍጡር/
The giant was as tall as a tree.
ግዙፉ ሰው ርዝመቱ ዛፍ ያክል ነበር።

*giraffe* (ጂራፍ)
ቀጭኔ/አንገቷ በጣም ረጅም የሆነ ዥንጉርጉር ቆዳ ያላት እንስሳ/
A giraffe has a long neck.
ቀጭኔ ረጅም አንገት አላት።



*girl* (ገል)
ልጃገረድ/ሴት ልጅ
The girls' volleyball team won their match.
የልጃገረዶቹ የመረብ ኳስ ቡድን ግጥሚያቸውን አሸነፉ።



*give* (ጊቭ)
መስጠት
My mother gave me money to buy some milk.
እናቴ ወተት እንድገዛ ገንዘብ ሰጠችኝ።

*glacier* (ግላሲየ)
ግግር በረዶ/ከተራራ በዝግታ የሚንሸራተት
The glacier moved slowly down the mountain.
ግግር በረዶው ከተራራው ላይ በዝግታ ተንሸራተተ።

*glad* (ግላድ)
መደሰት
After the long journey we were glad to arrive home.
ከረጅሙ ጉዞ በኋላ እቤት በመድረሳችን ደስተኞች ነበርን።

*glass* (ግላስ)
መስታወት
We use glass to make windows.
መስኮት ለመስራት መስታወት እንጠቀማለን።

*glasses* (ግላሲዝ)
ለማንበብ ወይም ለሀይ መከላከያነት አይናችን ላይ የምናደርገው /መነፅር/ የመስታወት ቁራጭ
My sister wears glasses for reading.
እህቴ ለማንበብ መነፅር ታደርጋለች።



*glide* (ግላይድ)
መንሸራተት
The boat glided across the water.
ጀልባው በውሀው ላይ ተንሸራተተ።

*globe* (ግለውብ)
ሉል/የአለም ካርታ የተሳለበት ክብ ነገር/
Can you find Ethiopia on the globe?
ኢትዮጵያን በሉል ላይ ማግኘት ትችላለህ?




*glove* (ግለቭ)
ጓንት/እጅ ላይ የሚጠለቅ ከጨርቅ ወይም ከቆዳ የሚሠራ
She wore gloves in the cold weather.
አየሩ ሲቀዘቅዝ የእጅ ጓንት አደረገች።



*go* (ገው)
መሄድ
We will go and buy the vegetables from the market.
አትክልቶችን ለመግዛት ገበያ እንሄዳለን።

*goal* (ገውል)
ጎል/ግብ/በስፖርት ጨዋታ
Melaku kicked the ball into the goal.
መላኩ ኳሷን ወደግብ መታት።

*goat* (ገውት)
ፍየል
Goats often have a strong smell.
ፍየሎች ብዙ ጊዜ ሀይለኛ ሽታ አላቸው።



***God*** (ጎድ)
1. እግዚአብሔር/የሁሉ ነገር ፈጣሪና ገዢ/ አምላክ
God is my shepherd.
እግዚአብሔር እረኛዬ ነው።
2. god

አማልክት/ጣኦት
Christians do not believe in other gods.
ክርስቲያኖች በሌሎች አማልክት አያምኑም።

*gold* (ገውልድ)
ወርቅ/ውድ የሆነ ሰዎች ለጆሮ፣ ለአንገትና ለእጅ ጌጥ የሚሰሩበት ማዕድን/
Gold can be found in rivers and under the ground.
ወርቅ በወንዝ ውስጥና በመሬት ውስጥ ይገኛል።

*good* (ጉድ)
1. ጎበዝ
He is a very good swimmer.
እሱ በጣም ጎበዝ ዋናተኛ ነው።
2. ጥሩ
Koyisa is a good boy.
ኮይሳ ጥሩ ልጅ ነው።

*goodbye* (ጉድባይ)
ደህና ሁን/ቻው ማለት/
She said, 'goodbye' to her mother.
እሷ እናቷን ደህና ሁኚ አለቻት።

*goods* (ጉድዝ)
የሚሸጡ/ የሚለወጡ ነገሮች
The goods were sent to the shop on a lorry.
የሚሸጡት ነገሮች በመኪና ወደሱቅ ተላኩ።

*gorilla* (ጎሪላ)
ትልቁና ሀይለኛው ጅራት የሌለው በአፍሪካ የሚገኝ ዝንጀሮ
Gorillas are very gentle as long as you do not make them angry.
ጉሬላዎች ካላናደዳችኋቸው በስተቀር በጣም ጨዋዎች ናቸው።



*graceful* (ግሬይስፍል)
ውብ ማራኪ/ደስ የሚያሰኝ እንቅስቃሴ/
She has graceful voice.
ማራኪ ድምፅ አላት።

*grade* (ግሬይድ)
የክፍል ደረጃ
She must be in grade 3 by now.
አሁን 3ኛ ክፍል መሆን አለባት።

*grandfather* (ግራንፋዘ)
የወንድ አያት/የእናት ወይም የአባት አባት
My grandfather died long ago.
አያቴ ከሞተ ብዙ ጊዜ ሆኖታል።

*grandmother* (ግራንመዘ)
የሴት አያት/የአባት ወይም የእናት እናት/
My grandmother is seventy years old.
አያቴ ሰባ አመቷ ነው።

*grandparent*(ግራንድፔየረንት)
አያት/ የእናትና የአባት ወላጅ
I love my grandparents.
አያቶቼን እወዳቸዋለሁ።

*grape* (ግሬይፕ)
ወይን/ትንንሽ ቀይ ቡኒ ቀለም ያለው የሚበላ ፍሬ
We can eat grapes or make them into wine.
ወይንን ፍሬውን ልንበላው ወይንም የወይን ጠጅ ልንሰራበት እንችላለን።



*grass* (ግራ፡ስ)
ሳር/መሬት ላይ የሚበቅል ለከብቶች ምግብነት የሚያገለግል አረንጓዴ ተክል
The cows ate the grass in the fields.
ላሞቹ ሜዳው ላይ ያለውን ሣር ጋጡት።



*grasshopper* (ግራስሆፐ)
ፌንጣ/የምትዘል ነፍሳት
The grasshopper jumped into the house.
ፌንጣዋ ወደ እቤት ውስጥ ዘላ ገባች።



*grateful* (ግሬይትፍል)
ማመስገን/ማድነቅ
The man was very grateful for the food.
ሰውየው ስለምግቡ በጣም አመስግኗል።

*gravy* (ግሬይቪ)
መረቅ
I like gravy on potatoes.
ከድንች ጋር መረቅ እወዳለሁ።

*grease* (ግሪ፡ስ)
ማጠጣት/መቀባት/ለማሽን/ የጠነከረ ነገርን ለማለስለስ የምንጠቀምበት ቅባት/ግራሶ/
We rubbed grease on his bicycle chain.
የብስክሌቱን ሰንሰለት ግራሶ ቀባነው።

*great* (ግሬይት)
ትልቅ ችሎታ ያለው/ታላቅ ሰው
That man is a great footballer.
ያ ሰውዬ ታላቅ የእግር ኳስ ተጫዋች ነው።

*greedy* (ግሪ፡ዲ)
ስግብግብ/በቃኝ የማይል/ ሁሉን ነገር ለራሱ ብቻ መውሰድ የሚፈልግ
Do not take any more candies.

You are a greedy boy.
ምንም ተጨማሪ ከረሜላ እንዳትወስድ አንተ ስግብግብ ልጅ ነህ።

*green* (ግሪ:ን)
አረንጓዴ ቀለም/የሳርና የቅጠሎች ቀለም
Apples can be green or red.
ፖሞች አረንጓዴ ወይም ቀይ ሊሆኑ ይችላሉ።



*grey* (ግሬይ)
ግራጫ
Elephants are grey.
ዝሆኖች ግራጫ ናቸው።

*grin* (ግሪን)
መገልፈጥ/ዝንጀሮኛ ሳቅ/ ከልብ ያልሆነ ሳቅ
When you grin you look ugly.
ስትገለፍጥ ታስጠላለህ።



*grind* (ግራይንድ)
መፍጨት ወደ ዱቄትነት መለወጥ
To make 'ingera' first we must grind the seed.
እንጀራ ለመጋገር መጀመሪያ እህሉን መፍጨት አለብን።

*grocer* (ግረውሰ)
የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ/ስኳር፣ ጨው የመሳሰሉ ነገሮች የሚሸጥበት ቦታ/
My mother sent me to the grocer to buy some tea and matches.
እናቴ ሻይቅጠልና ክብሪት እንድገዛ ወደሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ላከችኝ።



*ground* (ግራውንድ)
መሬት
The large tree fell to the ground.
ትልቁ ዛፍ መሬት ላይ ወደቀ።

*group* (ግሩ:ፕ)
ቡድን/ብዙ ሰዎች ወይም ነገሮች በአንድነት/
The teacher took a group of school children to the cinema.
አስተማሪው የተማሪዎችን ቡድን ወደ ሲኒማ ወሰደ።



*grow* (ግረው)
አበቀለ፣አደገ ቁመት፣እድሜ ጨመረ

We will grow cabbages in the garden this year.
በዚህ አመት በጓሮአችን ጎመን እናሳድጋለን።

*grown up* (ግረውን ኧፕ)
የደረሰ/ከ18 አመት በላይ የሆነ ሰው/
She has a grown-up son.
እሷ የደረሰ ልጅ አላት።

*guard* (ጋ:ድ)
ዘበኛ/የአንድ ቤት ግቢ/ቦታ ጠባቂ/
We have one guard to guard our house.
እቤታችንን የሚጠብቅ አንድ ዘበኛ አለን።



*guess* (ጌስ)
ግምት/አንድ ይሆናል ብለው ያሰቡትን ያሉትን መናገር/መላመምታት
Can you guess what is in this box?
በዚህ ሣጥን ውስጥ ምን እንዳለ መገመት ትችላለህ?

*guide* (ጋይድ)
አስጎብኚ/መንገድ የሚያሣይ የሚመራ/ መንገድ መሪ
The guide showed them the way over the mountain.
አስጎብኚው ወደ ተራራው የሚያወጣውን መንገድ አሣያቸው።

*guilty* (ጊልቲ)
ጥፋተኛ/ሀጢያተኛ/ተጠያቂ
The man was guilty of stealing the money.
ሰውየው ገንዘብ በመስረቁ ጥፋተኛ ሆነ።

*gum* (ገም)
ድድ/ጥርስ የሚበቅልበት ቦታ/
Your gums bleed when you lose your teeth.
ጥርስህን ስትነቅል ድድህ ይደማል።



*gun* (ገን)
ጠመንጃ/ማንኛውም ጥይት የሚተኩስ መሳሪያ
The man fired the gun in the air to make the birds go away.
ወፎቹን ለማባረር ሰውየው ጠመንጃ ወደ አየር ተኮሰ።




# Hh

*H, h* (ኤይች)
ስምንተኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*hair* (ሄየ)
ፀጉር
His mother told him to cut his hair.
እናቱ ፀጉሩን እንዲቆረጥ ነገረችው።




*half* (ሀ፡ፍ)
ግማሽ/እኩል ሁለት ቦታ ከተከፈሉ ቅሮች አንዱ
He took half of the orange and gave his sister half.
እሱ የብርቱካኑን ግማሽ ወስዶ ግማሹን ለእህቱ ሰጣት።



*hall* (ሆ፡ል)
አዳራሽ/ትልቅ ክፍል
The meeting was held in the town hall.
ስብሰባው የከተማው ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ ውስጥ ተካሄደ።

*hammer* (ሀመ)
መዶሻ/ሜፋ ከብረት የተሰራ እጀታ ያለው ምስማር መምቻ
He hammered the nails into the wood.
ምስማሮቹን እንጨቱ ውስጥ በመዶሻ መታቸው።



*hand* (ሀንድ)
እጅ/ መዳፍ እና ጣቶችን የሚይዘው የእጅ ክፍል
We can hold things with our hands.
በእጆቻችን እቃዎችን መያዝ እንችላለን።



*handkerchief* (ሀንከቺፍ)
መሀረብ/ለአፍንጫ ማበሻ የሚያዝ ቁራጭ ጨርቅ
Merga blew his nose on a red handkerchief.
መርጋ በቀይ መሀረብ አፍንጫውን ጠረገ።

*handle* (ሀንድል)
እጀታ/አንድን ነገር ለመያዝ
የሚያገለግል የበር ወይም የዶማ
መያዣ
The handle of the spade is broken.
የአካፋው እጀታ ተሰብሯል።

*handsome* (ሀንሰም)
ቆንጆ የሚስብ/የሚያምር/ማራኪ/ለወን
ድ ልጅ/
She had a handsome son with
brown eyes and curly hair.
ቡናማ አይንና የተጠቀለለ ፀጉር
ያለው ቆንጆ ልጅ አላት።

*hang* (ሀንግ)
አንድን ነገር ለማድረቅ ሽቦ ላይ
ወይም ገመድ ላይ ማንጠልጠል
I will hang the washing on the
line.
የታጠቡትን ልብሶች ገመድ ላይ እ
ሰቅላቸዋለሁ።

*happen* (ሀፐን)
የአንድ ነገር መሆን/መፈፀም መድረስ
The accident happened when it
was raining.
አደጋው የተከሰተው ዝናቡ ይዘንብ
በነበረበት ጊዜ ነው።
*happy* (ሀፒ)
ደስተኛ/ተደሳች
The children were very happy to
have a holiday.
ልጆቹ እረፍት በማግኘታቸው በጣም
ተደስተው ነበር።

*harbour* (ሀ:በ)
ወደብ/የመርከብ መቆሚያ ቦታ/የባህር
ዳርቻ/
There were ten big ships in the
harbour.
በወደቡ ላይ አስር ትልልቅ መርከቦች
ነበሩ።



*hard* (ሀ:ድ)
ለስላሳ ያልሆነ ጠንካራና
ጠጣር ነገር
He fall down on the hard rock
and hurt himself.
ጠንካራው አለት ላይ ወድቆ ተጎዳ።

*harvest* (ሀ:ቪስት)
አዝመራ መሰብሰቢያ/
የተዘራ እህል ለመለቀም ለመሰብሰብ
የሚደርስበት ጊዜ



My father will have a good maize harvest this year.
አባቴ በዚህ አመት ጥሩ የበቆሎ አዝመራ ይሰበስባል።

*has* (ሃዝ)
አለው/ አሉት/ አላት/ አሏት
He has two brothers.
እሱ ሁለት ወንድሞች አሉት።

*hat* (ሀት)
ኮፍያ/ለፀሀይ መከላከያ ጭንቅላት ላይ የሚደረግ ባርኔጣ
The girl's hat blew off in the wind.
የልጅቷ ኮፍያ በንፋስ ተወሰደ።



*hate* (ሄይት)
መጥላት/አንድን ነገር አለመውደድ/
I hate to clean my shoes every day.
ጫማዬን በየቀኑ መጥረግ ያስጠላኛል።

**have** (ሀቭ)
አለህ/አላቸው/አለን/አለሽ/አለኝ/አሉኝ
I have four goats and two cows.
አራት ፍየሎችና ሁለት ላሞች አሉኝ።

*hawk* (ሆ:ክ)
ጭልፊት/ተናጣቂ የወፍ ዘር
The hawk flew down and caught the rabbit in its claws.
ጭልፊቱ ወደታች በርሮ ጥንቸሏን በጥፍሮቹ ያዛት።

*hay* (ሄይ)
የደረቀ ሳር ክምር
After the harvest the barn will be full of hay.
አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ የከብቶቹ ቤት በሳር ድርቆሽ ይሞላል።

*head* (ሄድ)
ራስ፣ ጭንቅላት/ከአንገት በላይ ያለው የሰውነት ክፍል/
He has a big hat on his head.
ራሱ ላይ ትልቅ ኮፍያ አድርጓል።



*health* (ሄልዝ)
ጤና/ ከበሽታ ነፃ መሆን
Don't smoke cigarettes it's not good for your health.
ለጤናህ ጥሩ ስላልሆነ ሲጋራ አታጭስ።

*heap* (ሂ:ፕ)
ክምር/አንድ ቦታ ላይ የተከማቸና ከፍ ያለ ነገር/ቁልል/
Look at that heap of rubbish in the road.
ያንን በመንገድ ላይ ያለውን የቆሻሻ ክምር ተመልከት።

*hear* (ሂየ)
መስማት
I didn't hear what you say.
ምን እንዳልክ አልሰማውህም።

*heart* (ሀ:ት)
ልብ/የደም ዝውውርን የሚቆጣጠርልን የሰውነታችን ክፍል
He is an old man but he has a strong heart.
እሱ ሽማግሌ ነው ነገር ግን ጠንካራ ልብ አለው።



*heat* (ሂ:ት)
ሙቀት/ከፀሀይ/ከእሣት የምናገኘው/
The heat from the sun dried the clothes.
የፀሀይዋ ሙቀት ልብሶቹን አደረቃቸው።

*heaven* (ሄቨን)
ገነት/መንግስተ ሰማይ/በጣም ምቹና ደስ የሚል ቦታ
Some Christians believe that heaven will be on earth.
አንዳንድ ክርስቲያኖች ገነት መሬት ላይ ይሆናል ብለው ያምናሉ።

*heavy* (ሄቪ)
ከባድ/ ለመያዝ የማይቻል
It is hard to lift heavy things.
ከባድ ነገሮችን ማንሳት አስቸጋሪ ነው።

*hedge* (ሄጅ)
በጥድ ወይም በሌላ ዛፍ የተሰራ አጥር
My father is growing a hedge round our house.
አባቴ በቤታችን ዙሪያ ቁጥቋጦ ያሳድጋል።

*helicopter* (ሄሊኮፕተ)
ሄሊኮፕተር
The police followed the thieves in a helicopter.
ፖሊሶቹ ሌቦቹን በሄሊኮፕተር ተከታተሏቸው።



*hello* (ሀለው)
አሎ/ሀሎ ማለት
Hello is the only word used by almost every language in the world.
"ሀሎ" የአለም ቋንቋዎች ሁሉ የሚጠቀሙበት ብቸኛ ቃል ናት።

*helmet* (ሄልሜት)
/የብረት ባርኔጣ/ከብረት የሚሰራ

የጭንቅላት መከላከያ
Miners always wear helmets.
ማዕድን ቆፋሪዎች ዘወትር የራስ ቁር ያደርጋሉ።



*help* (ሄልፕ) ስ-
/ማገዝ/መርዳት/ ሌላ ሰው ሲሰራ አብሮ መስራት
Help your brother to carry that box.
ያንን ሳጥን ለመሸከም ወንድምህን እርዳው።

*hem* (ሄም)
ጠርዝ/የልብስ ጫፍ/
My uncle sewed the hem of my new dress.
አጎቴ የአዲሱ ቀሚሴን ጠርዝ ቀመቀመው።

*hen* (ሄን)
ሴት ዶሮ/ ለእንቁላል ወይም ለስጋ የምትረባ
All the hens laid eggs today.
ሁሉም ዶሮዎች ዛሬ እንቁላል ጥለዋል።

*herd* (ኸ፡ድ)
መንጋ/አንድ ላይ የሚሄዱ ብዙ እንስሳት/
The herd of cattle drank at the water hole.
የከብት መንጋው ከጉድጓድ ውሃ ጠጣ።



*here* (ሂየ)
እዚህ/ ተናጋሪው ሰው አጠገብ
Come here. I want to talk to you.
ወደእዚህ ና ላናግርህ እፈልጋለሁ።

*hero* (ሂየረው)
ጀግና/አንድ አስደናቂ ነገር የሠራ
The hero rescued the baby from the river.
ጀግናው ሰው ህፃኑን በወንዝ ከመወሰድ አዳነው።

*hide* (ሀይድ)
ተደበቀ/ደበቀ/ከእይታ ተሰወረ/
We can hide in the old cave.
በአሮጌው ዋሻ ልንደበቅ እንችላለን።

*high* (ሀይ)
ረጅም/ወደ ሰማይ ከፍ ያለ ከፍታ
The eagle flew high into the sky.
አሞራው በሰማይ ላይ ከፍ ብሎ በረረ።

*hill* (ሂል)
ኮረብታ/በአካባቢው ካለው መሬት ከፍ ያለ
You can see our village from the top of the hill.

ከኮረብታው ጫፍ ላይ የእኛን መንደር ለማየት ትችላለህ።



*hippopotamus* (ሂፐ'ፖተመስ)
ጉማሬ/በውሃ ውስጥ የሚኖር እውሬ
The hippopotamus lives in the river.
ጉማሬው ወንዝ ውስጥ ይኖራል።



*hiss* (ሂስ)
አፏጨ/ድምፅ አሰማ
The snake hissed because it was very angry.
እባቡ በጣም ተናዶ ስለነበረ አፏጨ።

*hit* (ሂት)
መምታት
The boy hit the ball into the river.
ልጁ ኳሱን ወደወንዙ ውስጥ መታው።

*hive* (ሃይቭ)
የንብ ቀፎ/ የንብ መኖሪያ
All the bees have left their hive.
ንቦቹ በሙሉ ቀፎአቸውን ለቀው ወጡ።

*hoe* (ኸው)
ገሶ/ ዲጂኖ/መሬት ለመቆፈሪያነት የሚያገለግል ብረት
The gardener used the hoe to dig out the weeds.
አትክልተኛው አረሞቹን ለመንቀል ገሶ ተጠቀመ።



*hold* (ኸውልድ)
በእጅ መያዝ ወይም ማቆየት
Please hold the baby for me.
እባክህ ህፃኑን ያዝልኝ።

*hole* (ኸውል)
ጉድጓድ ወይም ቀዳዳ
The men dug a hole in the street.
ሰዎቹ መንገዱ ላይ ጉድጓድ ቆፈሩ።


*holiday* ('ሆለዴይ)
እረፍት/በዓል/ትምህርት ወይም ስራ የማይሰራበት ቀን/አመት በዓል
We have a holiday on Saturday and Sunday.
እኛ ቅዳሜና እሁድ እረፍት አለን።

*home* (ኸውም)
ቤት/የሚኖሩበት ቦታ/
I want to go home to see my mother.
እናቴን ለማየት እቤት መሄድ እፈልጋለሁ።

*homework* ("ሆውምወ:ክ)
የቤት ሥራ/ እቤት ተወስዶ የሚሰራ ስራ
I always do my homework before I go out to play.
እኔ ሁልጊዜ ወደ ጨዋታ ከመሄዴ በፊት የቤት ስራዬን እሠራለሁ።

*honey* ("ሃኒ)
ማር/ንቦች የሚሠሩት በጣም የሚጣፍጥ ቢጫ ነገር/
I like honey and bread.
ዳቦ በማር እወዳለሁ።


*hoof* (ሁ:ፍ)
ኮቴ/ የከብቶች እግር ጠንካራው የታችኛው ክፍል
When the horse kicked him, its hoof hurt him.
ፈረሱ ሲረግጠው ኮቴው ጎዳው።



*hook* (ሁክ)
ሜንጦ/ግድግዳ ወይም እንጨት ላይ የሚመታ ጎበጥ ያለ ብረት ለማንጠልጠያነት የሚጠቅም
He bent the nail to make a hook.
ሜንጦ ለመስራት ምስማሩን አጎበጠው።



*hoop* (ሁ:ፕ)
ስፖርት ለመስራት እየዘለሉ የሚሾል ኩበት የብረት ቀለበት
The dog jumped through the burning hoop of the circus.
ውሻው ዙሪያውን በሚነደው የሰርከስ ቀለበት ውስጥ ዘለለ።



*hop* (ሁፕ)
እንጣጥ እንጣጥ ማለት
The girl hopped with one leg.
ልጅቷ በአንድ እግሯ እንጣጥ እንጣጥ አለች።

*hope* ("ሆውፕ)
ተስፋ ማድረግ/አንድን ነገር በጣም መፈለግ
I hope to get a bicycle for Christmas.
ለገና ብስክሌት እንደማገኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

*horn* (ሆ:ን)
ቀንድ/በከብቶች ጭንቅላት ላይ የሚበቅል ጠንካራና የሾለ ነገር/
Cows, goats and sheep have

horns.
ላሞች፣ ፍየሎችና በጐች ቀንድ አላቸው።

*horse* (ሆ፡ስ)
ፈረስ/ ለመጋለብ ወይም ጋሪ ለመጎተት የሚያገለግል እንስሳ/
The man rode his horse to bring the sheep.
ሰውየው በጉን ለማምጣት በፈረሱ ጋለበ።

*hose* (ኸውዝ)
ቱቦ/ለውሀ ማስተላለፊያነት የምንጠቀምበት መሀሉ ክፍት የሆነ ላስቲክ/
I need the hose to water the vegetables.
አትክልቶቹን ለማጠጣት የላስቲክ ቱቦ እፈልጋለሁ።

*hospital* (ሆስፒትል)
የታመሙ ሰዎች የሚታከሙበት ቦታ
Tolosa is in hospital with a broken leg.
ቶሎሳ እግሩ ተሰብሮ ሆስፒታል ነው።

*hot* (ሆት)
ሞቃት
Is the soup hot enough?
ሾርባው በደንብ ሞቅዋል?

*hotel* (ኸው'ቴል)
ሆቴል/ምግብ መጠጥና መኝታ በክፍያ የምናገኝበት ቦታ
We stayed in a very nice hotel for two days.
ለሁለት ቀናት ያህል በጣም ጥሩ ሆቴል ውስጥ ቆየን።

*hour* ('አወ)
ሰአት
The cake will take an hour to bake.
ኬኩን ለማብሰል አንድ ሰአት ይፈጃል።

*house* (ሀውስ)
ቤት
I like to live in that house.
እዛ ቤት መኖር ደስ ይለኛል።

*how* (ሀው)
እንዴት?
How did you fix that broken chair?
ያንን የተሰበረ ወንበር እንዴት ጠገንከው?

*howl* (ሀውል)
ከፍተኛ ጩኸት(የሀዘን/የስቃይ)፣ ማላዘን
The howl of the hyenas was very frightening.
የጅቦቹ ማላዘን በጣም አስፈሪ ነበር።

*hug* (ኸግ)
በፍቅር ሰውን ማቀፍ
When my mother saw her aunt, she ran and hugged her.
እናቴ አክስቷን ባየች ጊዜ ሮጣ አቀፈቻት።

*huge* (ህዩ፡ጅ)
ግዙፍ/ ትልቅ
They built a huge wall at the dam.
በግድቡ ላይ ትልቅ ግንብ ገነቡ።

*hum* (ˈሐም)
አፍን ገጥሞ ማዜም
The boy started to hum the song.
ልጁ አፉን ገጥሞ ዘፈኑን ማዜም ጀመረ።

*human* (ˈህዩ:መን)
የሰው ዘር
How many human beings are there on the earth?
በምድር ላይ ምን ያህል የሰው ዘሮች አሉ?

*hump* (ˈሐምፕ)
ሻኛ/አንዳንድ እንስሳት ጀርባ ላይ አብጦ የሚገኝ የሰውነት ክፍል
Camels have humps on their backs.
ግመሎች በጀርባቸው ላይ ሻኛ አላቸው።

*hundred* (ˈሐንድ:ረድ)
መቶ/100/
The distance from Addis Ababa to Adama is hundred kilometres.
ከአዲስ አበባ እስከ አዳማ ያለው ርቀት መቶ ኪሎ ሜትር ነው።

*hungry* (ˈሐንግሪ)
የተራበ
We eat when we are hungry.
ሲርበን እንበላለን።

*hurry* (ˈሐሪ)
መጣደፍ/ቶሎ ቶሎ መስራት ወይም መሄድ
Hurry or we will miss the bus.
ቶሎ ቶሎ በል አለበለዚያ አውቶቡሱ ያመልጠናል።

*hurt* (ˈሐ:ት)
የአካል መጎዳት
I hurt my knee when I fell.
ስወድቅ ጉልበቴን ተጎዳሁ።

*hut* (ˈሐት)
ጎጆ/ትኩል/የሣር ክዳን ያለው ቤት/
The farmer kept the hens in the hut.
ገበሬው ዶሮዎቹን ጎጆ ውስጥ አስገባቸው።

*hyena* (ሀይˈኢ:ነ)
ጅብ/በምሽት የሚሄድ ውሻ የመሰለ የዱር አውሬ/
The hyenas ate the dead zebra.
ጅቦቹ የሞተውን የሜዳ አህያ በሉት።

*hymn* (ሂም)
እግዚአብሔርን ለማሞገስ የሚዘመር መዝሙር
The children sang the hymn nicely.
ልጆቹ የምስጋና መዝሙሩን በጥሩ ሁኔታ ዘመሩ።

*I, i* (አይ)
1. ዘጠነኛው የእንግሊዝኛ ፊደል
2. እኔ

I am a student.
እኔ ተማሪ ነኝ።

*ice* (አይስ)
በረዶ/በጣም የቀዘቀዘና የጠጠረ በረዶ
The sun has melted the ice.
ፀሃይዋ በረዶውን አቀለጠችው።



*Ice cream* (አይስ ክሬም)
ከወተት፣ ከቾኮሌት የሚሠራ ቀዝቃዛና የሚላስ ነገር
I like Ice cream very much.
አይስክሬም በጣም እወዳለሁ።



*idea* (አይ'ዲየ)
ሃሣብ/ ከአዕምሮ የሚወጣ ነገር
It was a good idea to bring a drink with us.
የሚጠጣ ነገር ይዘን መምጣታችን ጥሩ ሃሣብ ነበር።

*idiot* (ኢዲየት)
በጣም ጅል የሆነ ሰው
She is behaving like an idiot.
ድርጊቷ እንደ ጅል ሰው ነው።

*ill* (ኢል)
መታመም
After eating all the bananas Gebrai felt ill.
ሁሉንም ሙዞች ከበላ በኋላ ገብሬይ ህመም ተሰማው።

*impossible* (ኢም'ፖሰብል)
ለማድረግ የማይቻል ነገር
It is impossible for me to be home by eight o'clock.
በሁለት ሰዓት እቤት መግባት ለኔ የማይቻል ነገር ነው።

*improve* (ኢም'ፕሩ፡ቭ)
ማሻሻል/ማስተካከል/ማሳመር
The new carpet will improve this room.
አዲሱ ምንጣፍ ይህን ክፍል ያሳምረዋል።


*in* (ኢን)
ውስጥ/ አንድ ነገር ውስጥ መሆን
The boy is in the house.
ልጁ ቤት ውስጥ ነው።

*include* (ኢንክሉ፡ድ)
በቡድን ውስጥ ማስገባት ማጠቃለል
We will include Tola in the team.

ቶላን ቡድኑ ውስጥ እናስገባዋለን።

*indoors* (ኢን'ዶ:ዝ)
ቤት ውስጥ/ውስጥ
When it started to rain we ran indoors.
ዝናብ መዝነብ ሲጀምር ወደቤት ውስጥ ሮጥን።

*infant* ('ኢንፌንት)
ህጻን/ከአንድ አመት በታች የሆነ/
All the infants were crying.
ሁሉም ህጻናት ያለቅሱ ነበር።



*infectious* (ኢን'ፌክሽስ)
ተላላፊ በሽታ/ከሰው ወደ ሰው የሚተ-ላለፍ በሽታ/
Measles is a very infectious sickness.
ጉድፍ በጣም ተላላፊ የሆነ በሽታ ነው።

*inform* (ኢን'ፎ:ም)
ለአንድ ሰው አንድ ነገር መንገር
The policeman informed us that the road was closed.
ፖሊሱ መንገዱ ዝግ እንደሆነ ነገረን።

*initial* (ኢ'ኒሽል)
የመጀመሪያ የስማችን ፊደል
The initial of my first name is J.
የስሜ የመጀመሪያ ፊደል J ነው።


*injection* (ኢን'ጄክሽን)
ክትባት/የበሽታ መከላከያ መድሃኒት ወደ ሰውነት ውስጥ በመርፌ ማስገባት/
The doctor gave me an injection against polio.
ሀኪሙ የፖሊዮ መከላከያ ክትባት ከተበኝ።

*ink* (ኢንክ)
ቀለም ያለው ፈሳሽ ለመጻፊያነት የምንጠቀምበት
She wrote her letters in black ink.
ደብዳቤዎቿን በጥቁር ቀለም ፃፈች።



*innocent* ('ኢነሰንት)
ምንም ጥፋት የሌለበት ንፁህ
The man didn't steal the car. He is innocent.
ሰውየው መኪናውን አልሰረቀም። ንፁህ ነው።

*insect* ('ኢንሴክት)
ነፍሳት/ስድስትና ከዛ በላይ እግር ያላቸው ትንንሽ እንስሳት
Flies, ants, butterflies and bees are all insects.
ዝንቦች፣ ጉንዳኖች ቢራቢሮዎች እና ንቦች ሁሉም ነፍሳት ናቸው።



*inside* (ኢን'ሳይድ)
**ከአንድ ነገር ውስጥ/ከውጭ ሳይሆን**
There are six rooms inside the building.
**በህንፃው ውስጥ ስድስት ክፍሎች አሉ።**

*interest* ('ኢንትረስት)
**ፍላጎት/አንድን ነገር መፈለግ/**
She is interested in singing.
**የመዝፈን ፍላጎት አላት።**

*into* ('ኢንቱ፡)
**ወደ ውስጥ**
Please get into the house.
**እባክህ ወደ ቤት ግባ**

*invent* (ኢን'ቬንት)
**መፈልሰፍ/መፍጠር/ አስቦ አስቦ አንድ ከዚህ በፊት በአለም የሌለ ነገር መስራት/**
Doctor Aklilu Lema invented new medicine for bilharzia.
**ዶክተር አክሊሉ ለማ ለቢልሃርዚያ በሽታ አዲስ መድሃኒት ፈለሰፉ።**

*invisible* (ኢን'ቪዚብል)
**ስውር/በአይን ሊታይ የማይችል ነገር**
The plane is so high in the sky that it is invisible.
**አይሮፕላኑ በጣም ወደ ሰማይ ስለራቀ በአይን አይታይም።**

*invite* (ኢን'ቫይት)
**አንድ ሰው አንድ ነገር እንዲሰራ መጋበዝ**
Can I invite my friend to stay for the weekend?
**ጓደኛዬ ቅዳሜና እሁድን እንዲቆይ መጋበዝ እችላለሁ?**


*iron* ('አይየን)
1. **ብረት**
The cooking pot is made of iron.
**የመቀቀያ ድስቱ የተሰራው ከብረት ነው።**
2. **ስሩ ጠፍጣፋ ሆኖ መያዣ ያለው የልብስ መተኮሻ/ካውያ**
Mother, please tell me where the iron is.
**እማዬ እባክሽ ካውያው የት እንደሆነ ንገሪኝ።**
3. **ልብስን መተኮስ**
Dad, please iron my shirt.
**አባባ እባክህ ሸሚዜን ተኩስልኝ።**

*is* (ኢዝ)
**ነው/ የአንድ ነገር መሆንን የሚያመለክት**
This is a cat.
**ይህ ድመት ነው።**

*island* ('አይለንድ)
ደሴት/ዙሪያውን በውሃ የተከበበ ደረቅ መሬት/
Australia is the largest island in the world.
አውስትራሊያ በአለም ትልቁ ደሴት ነው።

*itch* (ኢች)
ሽፍታ/ሰውነት ላይ የሚያሳክክ ነገር/
The dog scratched the itch on its back.
ውሻው ጀርባው ላይ ያለውን ሽፍታ አከከው።

*ivory* ('አይቮሪ)
የዝሆን ጥርስ
Many elephants are killed for their ivory.
ብዙ ዝሆኖች ለጥርሳቸው እየተባለ በሰዎች ይገደላሉ።



*J j* (ጄይ)
አሥረኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*jackal* (ጃኮ:ል)
ቀበሮ/ውሻ የመሰለ የዱር አውሬ/
The jackals waited until the lions had finished eating.
ቀበሮዎቹ አንበሶቹ በልተው
እስኪያበቁ ጠበቁ።



*jacket* (ጃኪት)
ኮት/ከወገብ በላይ የሚለበስ ከፊቱ
የሚከፈት ልብስ
Awel wore his jacket and went to school.
አወል ኮቱን ለብሶ ትምህርት ቤት
ሄደ።



*jaguar* (ጃግዩወ)
ጃጉዋር/ነብርንጉርጉር የድመት ዘር የዱር
አውሬ/
Jaguars live in South America.
ጃጉዋሮች የሚኖሩት በደቡብ
አሜሪካ ነው።


*jam* (ጃም)
1. ማርማላታ/ከስኳርና ከፍራፍሬ የሚ
ሰራ ጣፋጭ
I like bread and jam.
ዳቦ በማርማላታ እወዳለሁ።
2. በመኪና ወይም በሰው ብዛት
ምክንያት ቶሎ ቶሎ መሄድ
አለመቻል/ መጨናነቅ
The man missed the train because of the traffic jam.
በሰውና በመኪናው መጨናነቅ
ምክንያት ሰውየው ባቡሩ አመለጠው።

*January* (ጃንዩወሪ)
ጥር/በጎርጎርሣውያን የአመቱ
የመጀመሪያ ወር በኢትዮጵያውያን
የአመቱ 5ኛ ወር/
January comes after December.
ጥር ከታህሳስ ቀጥሎ
ይመጣል።

*jar* (ጃ:)
ብልቃጥ/ከመስተዋት ወይም ከሸክላ
የተሰራ ፈሳሽ ወይም ዱቄት መያዣ/
Mother made the jam. Then she put it into the jar.
እማዬ ማርማላቱን ሰርታ ብልቃጡ
ውስጥ አስቀመጠችው።



*jaw* (ጆ:)
መንጋጋ/ጥርስን ከሚይዙ አጥንቶች አንዱ መንጋጭላ
The boxer hit him on the jaw.
ቦክሰኛው መንጋጭላውን መታው።



*jealous* ('ጄለስ)
መቅናት/የሌላውን ሰው አንድ ጥሩ ነገር ሲሰራ ወይ ሲገዛ ያንን ለራስ ለማድረግ መፈለግ
Abebe is jealous because his brother has a new bicycle.
አበበ ወንድሙ አዲስ ብስክሌት ስላለው ቀና።

*jersey* ('ጀ:ዚ)
ሹራብ/ከበግ ፀጉር የሚሰሩ ከወገብ በላይ የሚለበሱ ልብሶች/
My father is wearing his new jersey over his shirt.
አባቴ ከሸሚዙ ላይ አዲሱን ሹራቡን ለብሷል።


*jet* (ጄት)
1. በጠባብ ቀዳዳ ሾልኮ የሚወጣ ፈጣን ፈሳሽ/ የሚወረወር ውሃ/ ያፈተለከ
The jet of water shot up into the sky.
ያፈተለከው ውሃ ወደ ሰማይ ተወረወረ
2. ጀት/ በጣም ፈጣን አይሮፕላን/
The jet plane flew quickly across the sky.
ጀት አይሮፕላኑ በፍጥነት ሰማዩን አቋርጦ በረረ።



*jewel* ('ጁወ:ል)
እንቁ/አልማዝ
Jewels are the most expensive stones.
አልማዞች ከሁሉ በላይ ውድ ድ ንጋዮች ናቸው።

*jewellery* (ጁወ:ለሪ)
ጌጣ ጌጦች/እንገት፣ ጆሮ፣ጣት ላይ የሚደረጉ
I like jewellery.
ጌጣጌጥ እወዳለሁ።

*jigsaw* ('ጂግሶ:)
ቅርፅ ማውጫ መጋዝ
The carpenter has a jigsaw.
አናጺው ቅርፅ ማውጫ መጋዝ አለው።



*job* (ጆብ)
ገንዘብ እየተከፈለ የሚሰራ ስራ
What is your father's job?
የአባትህ ስራ ምንድነው?

*join* (ጆይን)
1. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን ማገናኘት ማጋጠም
We joined the pieces of wood together with glue.
ቁራጭ እንጨቶቹን በማጣበቂያ አጣበቅናቸው።
2. የአንድ ቡድን አባል መሆን
I am going to join the church choir.
የቤተክርስቲያን ዘማሪዎች ቡድን አባል ልሆን ነው።

*joint* (ጆይንት)
ሁለት ነገሮች የሚገጣጠሙበት ቦታ
The ankle is the joint between the foot and the leg.
ቁርጭምጭሚት እግርና ቅልጥም የሚገናኙበት ቦታ ነው።

*joke* (ጆውክ)
አንድ ነገር በመናገር ወይም በመስራት ሰዎችን ማሳቅ
Dad always tells us jokes
አባባ ሁልጊዜ ቀልዶችን ይነግረናል።

*jolly* (ጆሊ)
ደስተኛ
She is a very jolly person.
እሷ በጣም ደስተኛ ሰው ናት።

*journey* (ጀ:ኒ)
ከአንድ ቦታ ተነስቶ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ/መጓዝ/
We had a journey to Bahirdar last week.
ባለፈው ሳምንት ወደ ባህርዳር ተጉዘን ነበረ።

*joy* (ጆይ)
ደስታ
He jumped with joy at the good news.
መልካሙን ዜና ሲሰማ በደስታ ዘለለ።

*judge* (ጃጅ)
1. ዳኛ/በፍርድ ቤት የአንድን ድር ጊት ትክክል መሆንና መሳሳትን የሚወስን የተሳሳተውን የሚቀጣ ሰው
The judge sent the thief to prison.
ዳኛው ሌባውን ወደ እስር ቤት ላኩት።



2. መወሰን/ጥሩ የሆነውን መምረጥ
You must judge the best cow.
ጥሩዋን ላም መምረጥ አለብህ።

*juggler* (ጃግል)
ጃግላር/የሰርከስ ትርኢት ለማሳየት ኳሶችን ወደላይ እያቀባበለ የሚይዝ

ሰው/
The juggler threw three plates in the air and caught them one by one.
ጃግላሩ ሶስት ሰሃኖችን ወደ ላይ ወርውሮ አንድ በአንድ ቀለባቸው።



*juice* (ጁ:ስ)
የፍራፍሬ ጭማቂ
He likes to drink pineapple juice.
የአናናስ ጭማቂ መጠጣት ይወዳል።



*July* (ጁላይ)
ሀምሌ/በጎርጎርሣውያን የአመቱ 7ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 11ኛ ወር
July comes after June.
ሐምሌ ከሰኔ በሁዋላ ይመጣል።

*jump* (ጀምፕ)
መዝለል/አንድን ነገር ዘሎ ማለፍ/
The thief jumped over the wall.
ሌባው የግንብ አጥሩን ዘለለው።



*June* (ጁ:ን)
ሰኔ/በጎርጎርሣውያን የአመቱ 6ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 10ኛ ወር/
June comes after May.
ሰኔ ከግንቦት በሁዋላ ይመጣል።

*jungle* (ጀንግል)
ደን/ ብዙ ዛፎች በአንድነት የሚበቅሉበት ቦታ/
Monkeys live in the jungle.
ዝንጀሮዎች በደን ውስጥ ይኖራሉ።



*junior* (ጁ:ኒየ)
ትንሽ/ለክፍል ደረጃ ወይም ለእድሜ/
Primary schools are for junior children.
አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለትናንሽ ልጆች ናቸው።

# Kk

*K,k*(ኬይ)
አስራ አንደኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*keep* (ኪ:ፐ)
አንድን ነገር ማስቀመጥ/ መያዝ
I keep my handkerchief in my pocket.
መሀረቤን ኪሴ ውስጥ እይዛለሁ።

*kennel* ('ኬንል)
ለውሾች መኖሪያ የሚሰራ ትንሽ ቤት
I made a kennel for my new dog.
ለአዲሱ ውሻዬ ቤት ሰራሁለት።




*ketchup*('ኬቸፕ)
ከቲማቲም ጭማቂ የሚሰራ ስጎ
I like tommato ketchup with fish.
ከአሳ ጋር የቲማቲም ስጎ እወዳለሁ።



*kettle* ('ኬትል)
ጀበና/ማንቆርቆሪያ/ከብረት የሚሰራ የውሃ ማፍያ/
She boiled water in the kettle to make some tea.
ሻይ ለማፍላት በማንቆርቆሪያ ውሃ አፈላች።




*key*(ኪ)
ቁልፍ /የተቀረፀ ቁራጭ ብረት/ የተቆለፈ ነገር መክፈቻ
Use the key to open the car door.
የመኪናውን በር ለመክፈት ቁልፉን ተጠቀም።



*kick*(ኪክ)
መጠለዝ/በእግር መምታት/
She kicked the ball.
ኳሱን ጠለዘችው።



*kid* (ኪድ)
ወጠጤ/የፍየል ልጅ/
The kid played with the other goats in the field.
ወጠጤው ከሌሎች ፍየሎች ጋር ሜዳ ላይ ቦረቀ።



*kidnap* (ኪድናፕ)
ማፈን/አንድን ሰው በግድ መያዝ/
The thieves kidnapped the rich man's child.
ሌቦቹ የሃብታሙን ሰው ልጅ አፈኑት።

*kill* (ኪል)
መግደል/በህይወት እንዳይቆይ ማድረግ/
The hunter killed the elephant.
አዳኙ ዝሆኑን ገደለው።


*kilogram* (ኪሎግራም)
የክብደት መለኪያ/ኪሎግራም/
She bought five kilograms of sugar.
አምስት ኪሎግራም ስኳር ገዛች።

*kilometre* (ኪሎሜትር)
የርቀት መለኪያ
They live five kilometres from the town.
ከከተማው አምስት ኪሎ ሜትር ርቀው ይኖራሉ።

*kind* (ካይንድ)
1. ጥሩ/ደግ/ሩህሩህ ሰው
She is kind to sick people.
ለታመሙ ሰዎች ደግ/ሩህሩህ ናት።
2. አንድ አይነት ነገር
Toyota is a kind of car.
ቶዮታ የመኪና አይነት ነው።

*king* (ኪንግ)
ንጉስ/አገር የሚመራ
Haileselassie was the last king of Ethiopia.
ኃይለስላሴ የመጨረሻው የኢትዮጵያ ንጉስ ነበሩ።

*kingfisher* (ኪንግ)
የወንዝ አሞራ/አሳ በሊታ ከወንዝ አካባቢ የሚኖር ወፍ
The kingfisher dived into the river to catch the fish.
የወንዝ አሞራው አሳውን ለመያዝ ወደ ወንዙ ውስጥ ተወርውሮ ገባ።




*kiss* (ኪስ)
መሳም/አንድን ሰው በከንፈር መንካት
The girl kissed her uncle.
ልጅቷ አጎቷን ሳመችው።



*kitchen* (ኪችን)
ማእድ ቤት
My mother is cooking food in the kitchen.
እናቴ ማእድ ቤት ውስጥ ምግብ እያበሰለች ነው።




*Kte* (ካይት)
ወላንዶ/ከወረቀት ተሰርቶ በረጅም ገመድ የሚያዝ ተንሣፋፊ የልጆች መጫወቻ
The wind blew the kite into the tree.
ንፋሱ ወላንዶውን ወደ ዛፉ ወሰደው።




*kitten* ('ኪትን)
ሙጭሊት/የድመት ግልገል/
The mothei cat had six kittens.
እናትየዋ ድመት ስድስት ሙጭሊቶች ነበሯት።



*knee* (ኒ፡)
ጉልበት የእግር ማጠፊያ/
He hurt his knee playing football.
ኳስ ሲጫወት ጉልበቱ ታመመ።



*knife* (ናይፍ)
ቢላ/ስለታም ለመቆራረጥ የሚጠቅም የማእድ ቤት እቃ
He cut the meat with the knife.
ስጋውን በቢላ ቆረጠው።



*knit* (ኒት)
በኪሮሽ ሹራብ ዳንቴል መስራት
Mom used green wool to knit me a scarf.
እማዬ ያንገት ልብስ ልትሰራልኝ አረንጓዴ ክር ተጠቀመች።



*knock* (ኖክ)
ማንኳኳት
He knocked at the door very loudly.
በሩን በሃይል አንኳኳው።


*knot* (ኖት)
ቋጠሮ/ገመድ ወይም ክር እርስ በርስ የተጠላለፈበት ቦታ/
She tied the rope in a knot.
ገመዱን ቋጠረችው።



*know* (ነው)
1. ማወቅ/አንድን ነገር ወይም ሰው ማስታወስ/
Do you know that man?
ያንን ሰው ታውቀዋለህ?
2. አንድን ነገር እንዴት እንደሚደረግ መረዳት ማወቅ
I know the way to make a kite.
ወላንዶ እንዴት እንደሚሰራ አውቃለሁ።

*knowledge* (ኖሊጅ)
እውቀት
His knowledge of Science is very good.
የሳይንስ እውቀቱ በጣም ጥሩ ነው።

*knuckle* (ነክል)
ጣቶች ከመዳፍ ጋር የሚገናኙበት
He hurt his knuckles hitting the door.
በሩ ሲገጨው የጣቱ መገጣጠሚያዎች ተጎዱ።




# Ll

*L,l* (ኤል)
አስራ ሁለተኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*label* ('ሌይብል)
ምልክት/ስምና የተሰራበት አገር የተፃፈበት ወረቀት (እቃው ላይ የሚለጠፍ)
The label on the tin says fire extinguisher.
በቆርቆሮው ላይ ያለው ምልክት የእሳት ማጥፍያ ይላል።



*lace* (ሌይስ)
የጫማ ማሰሪያ ክር
He broke his shoe lace.
የጫማ ማሰሪያውን በጠሰው።




*ladder* ('ላደ)
መሰላል/በእንጨት ወይም በብረት የሚሰራ ከፍ ወዳለ ነገር ላይ መውጫ
He climbed the ladder to repair the roof.
ጣራውን ለመጠገን በመሰላል ወጣ።



*lady* ('ሌይዲ)
ሴት ወይዘሮ/ያገባች ሴት/
The kind lady gave us something to drink.
ደግ ሴት የምንጠጣው ነገር ሰጠችን።

*lake* (ሌይክ)
ሀይቅ/አንድ ቦታ የተጠራቀመ ሰፊ ውሃ የማይንቀሳቀስ
We crossed the lake with a small boat.
ሀይቁን በትንሽ ጀልባ አቋረጥነው።



***lamb*** (ላም)
ጠቦት/በጣም ትልቅ ያልሆነ የበግ ግልገል/

The lamb's wool is very soft.
የጠቦቱ ፀጉር በጣም ለስላሳ ነው።



*lame* (ሌይም)
የአካል ጉዳተኛ/ እግሮቹ መንቀሳቀስ የማይችሉ
She was lame for a long time after the accident.
ከአደጋው በኋላ ለረጅም ጊዜ እግሮቿ መንቀሳቀስ አይችሉም ነበር።

*lamp* (ላምፕ)
ፋኖስ/በኤሌክትሪክ ሃይል ወይም በጋዝ የሚሰራ ብርሃን የሚሰጥ/
Lamp is a usual source of light in Ethiopia.
ፋኖስ በኢትዮጵያ የተለመደ የብርሃን ምንጭ ነው።



*land* (ላንድ)
1. የመሬት ደረቅ ክፍል
The land here is covered with rocks.
እዚህ ያለው መሬት በአለቶች የተሸፈነ ነው።
2. ከአየር መሬት ላይ ማረፍ
The plane landed at the airport.
አውሮፕላኑ በአየር ማረፊያው አረፈ።

*lane* (ሌይን)
ጠባብ መንገድ
They drove along the lane to the farm.
ወደ እርሻው ቦታ በጠባቡ መንገድ ነዱ።



*language* (ላንግዊጅ)
ቋንቋ/ ሰዎች የሚነጋገሩበት
In Ethiopia there are about eighty languages.
በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ሰማንያ የሚሆኑ ቋንቋዎች አሉ።

*large* (ላ:ጅ)
ትልቅ
A mountain is larger than a hill.
ተራራ ከኮረብታ ይተልቃል።

*last* (ላ:ስት)
መጨረሻ/ ከሁሉ በኋላ
He came last in the race.
በውድድሩ የመጨረሻ ሆነ።

*late* (ሌይት)
መዘግየት/መድረስ ከሚገባው ጊዜ ማሳለፍ/
The train was two hours late.
ባቡሩ ሁለት ሰአታት ዘግይቶ ነበር።

*laugh* (ላ:ፍ)
ሳቅ
They laughed at their teacher's joke.
በአስተማሪያቸው ቀልድ ሳቁ።

*laundry* (ሎ:ንድሪ)
የልብስ ንጽህና መስጫ/ገንዘብ ተከፍሎ ልብስ የሚታጠብበት ቦታ
He took his dirty cloth to the laundry.
የቆሸሸ ልብሱን ወደ የልብስ ንጽህና መስጫ ቤት ወሰደ።

*law* (ሎ:)
ህግ/ለአንድ ህዝብ መተዳደሪያ መመሪያነት/በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚወጣ/
Driving at 160 Km an hour is against the law.
በሰአት 160 ኪሎ ሜትር መንዳት ህግን መጣስ ነው።

*lawn* (ሎ:ን)
በደንብ የተያዘ የሳር መስክ
The children played with the ball on the lawn.
ልጆቹ በሳር መስኩ ላይ ኳስ ተጫወቱ።

*lay* (ሌይ)
1. አንድ ቦታ ላይ ማስቀመጥ/ማቅረብ
He help me lay the table.
ጠረጴዛ በማቀራረብ እረዳኝ።
2. ለዶሮ/ለወፎች እንቁላል ጣለች ለማለት
The hens lay eggs everyday.
ዶሮዎቹ በየቀኑ እንቁላል ይጥላሉ።

*lazy* (ሌይዚ)
ሰነፍ/ስራ የማይወድ/
The lazy boy let his brother do all the work.
ሰነፉ ልጅ ሁሉንም ስራ ወንድሙ እንዲሰራው አደረገ።

*lead* (ሌድ)
1. እርሳስ/ ቀላጭ ብረት/
The water pipes were made of lead.
የውሀ ቧንቧዎቹ ከቀላጭ ብረት/ ከእርሳስ ነው የተሰሩት።
2. መምራት/መንገድ ማሳየት/
Follow the arrows they will lead you to the museum.
ቀስቶቹን ተከተል ወደ ሙዚየሙ ይመሩሃል።

*leaf* (ሊ:ፍ)
ቅጠል
Only one leaf failed from the tree.
ከዛፉ የወደቀች አንዲት ቅጠል ብቻ ናት።



*leak* (ሊ:ክ)
መንጠባጠብ
The water is leaking from that bucket.
ከዛ ባልዲ ውስጥ ውሃው እየተንጠባጠበ ነው።

*lean* (ሊ:ን)
መደገፍ
Do not lean against the window.
መስታወቱን አትደገፈው ::

*learn* (ለ:ን)
መማር/አንድ ነገር ማድረግን ማወቅ/
Do you want to learn how to swim?
እንዴት መዋኘት እንደሚቻል መማር ትፈልጋለህ?

*leather* ('ሌዘ)
ቆዳ
My mother bought a leather handbag.
እናቴ የቆዳ የእጅ ቦርሳ ገዛች።

*leave* (ሊ:ቭ)
1. ከአንድ ቦታ ለቆ መሄድ
When will you leave school?
መቼ ነው ትምህርት ቤት የምትለቀው?
2. ማስቀመጥ መተው
I will leave you two chocolates.
ሁለት ቼኮላት አስቀምጥልሀለሁ።

*leek* (ሊ:ክ)
ባሮ ሽንኩርት/ከነቅጠሉ ለወጥ ማጣፈጫነት የሚያገለግል የሽንኩርት አይነት/
Mother put leeks in the soup.
እናቴ ሾርባው ውስጥ ባሮ ሽንኩርት ትጨምራለች።



*left* (ሌፍት)
ግራ
Hold the book in your left hand.
መጽሀፉን በግራ እጅህ ያዘው።

*leg* (ሌግ)
እግር/የምንራመድበት የሰውነት ክፍላችን
Lions have four legs.
አንበሶች አራት እግሮች አሏቸው።

*lemon* ('ሌመን)
ሎሚ/ሲበሉት የሚኮመጥጥ አረንጓዴ ክብ ፍሬ/
We have a lemon tree in our garden.

በአትክልት ቦታችን ውስጥ የሎሚ ዛፍ አለን።



*lend* (ሌንድ)
ማዋስ/አንድን ነገር ከተጠቀሙበት በኋላ እንዲመልሱ መስጠት
I will lend you the book until tomorrow.
መፅሀፉን እስከነገ አውስሀለሁ።

*length* (ሌንግዝ)
ርዝመት/የአንድ ነገር ቁመት/
The road is five kilometres in length.
የመንገዱ ርዝመት አምስት ኪሎ ሜትር ነው።

*leopard* ('ሌፐድ)
አቦ ሸማኔ/እንደ ነብር ዥንጉርጉር የሆነ የዱር እንስሳ/
It is hard to see leopards in the long grass.
በረጃጅም ሳሮች ውስጥ አቦሸማኔዎችን ማየት አስቸጋሪ ነው።




*less* (ሌስ)
ከታሰበው ወይም ከተገመተው ያነሰ
They are arriving in less than an hour.
ከአንድ ሰአት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ይደርሳሉ።

*lesson* ('ሌሰን)
ትምህርት/ስለ አንድ ነገር መማር/
We had a History lesson this morning.
ዛሬ ጠዋት የታሪክ ትምህርት ነበረን።

*let* (ሌት)
አንድ ነገር እንዲሆን መፍቀድ
The teacher let them play football.
መምህሩ እግር ኳስ እንዲጫወቱ ፈቀዱላቸው።

*letter* ('ሌተ)
1. የአንድ ቋንቋ ፊደላት
A B C and D are letters.
ኤ፣ቢ፣ሲ እና ዲ ፊደላት ናቸው።
2. ደብዳቤ
I wrote my friend a letter.

ለጓደኛዬ ደብዳቤ ፃፍኩለት።



*lettuce* (ሌ·ቲየስ)
ሰላጣ/ጥሬውን የሚበላ የአትክልት አይነት/
My father grows lettuce, tomatoes and spinach.
አባቴ ሰላጣ፣ ቲማቲምና ቆስጣ ያበቅላል።

*level* (ሌ·ቨል)
ከፍና ዝቅ ያለ ቦታ የሌለው የተስተካከለ ቦታ
A ground for the football field must be levelled.
ለእግር ኳስ ሜዳነት የሚያገለግል መሬት እኩል የተስተካከለ መሆን አለበት።

*liar* (ላይየ)
ውሸታም/የሆነውን ትቶ ያልሆነውን የሚናገር/
He is a liar he said he did not steal the book.
ውሸታም ነው መጽሃፉን አልሰረቅሁም አለ።

*library* (ላይብረሪ)
ቤተ መጸሀፍት/ብዙ መጸሀፍት የሚገኙበት ሰዎች የሚያነቡበት ቤት
Every afternoon I go to the library.
ሁልጊዜ ከሰአት ወደ ቤተ-መፃሀፍት እሄዳለሁ።



*lick* (ሊክ)
በምላስ መላስ
The cow licked the calf.
ላሟ ጥጃውን ላሰችው።

*lid* (ሊድ)
እፊያ/አክንባሎ የአንድ ነገር ክዳን
Put the lid back on the pot.
የገንቦውን ክዳን መልሰህ ክደነው።

*lie* (ላይ)
1. መዋሸት/የሆነውን ትቶ ያልሆነውን መናገር/
He is telling a lie. I did not break the cup.
ውሸት እየተናገረ ነው። እኔ ሲኒውን አልሰበርኩም።
2. ተንጋለለ/በጀርባው ተኛ/

Lie down and rest on the bed.
አልጋው ላይ ተንጋለልና አረፍ በል።

*life* (ላይፍ)
ህይወት
You are five years old. Your life has only started.
አምስት አመትህ ነው። ህይወትህ ገና መጀመሩ ነው።

*lift* (ሊፍት)
1. አሳንሰር/በእግራችን ሳንራመድ ወደ ፎቅ የሚያስወጣን መሳሪያ/
The lift took us up to the office on the tenth floor.
አሳንሰሩ አስረኛ ፎቅ እስካለው ቢሮ ወሰደን።
2. አንድን ነገር ከነበረበት ማንሳት
The boy lifted the bag of maize easily.
ልጁ ጆንያ ሙሉ በቆሎውን በቀላሉ አነሳው።

*light* (ላይት)
1. ቀላል ብዙ ክብደት የሌለው
She is as light as a feather.
እንደ ዶሮ ላባ ቀላል ነች።
2. እሳት ማቀጣጠል ወይም ሻማ መለኮስ
Please light the fire, it is very cold.
እባክህ እሳቱን አቀጣጥለው በጣም ይበርዳል።
3. ብርሃን
We can all see by the light of the sun.
በፀሀይ ብርሀን ሁላችንም ማየት እንችላለን።

*like* (ላይክ)
1. መምሰል/ሌላውን የሚመስል/
He looks just like his brother.
እርሱ ልክ ወንድሙን ይመስላል።
2. መውደድ
I like orange very much.
ብርቱካን በጣም እወዳለሁ።

*limp* (ሊምፕ)
ማንከስ/አንድ እግርን በግድ እያነሱ መራመድ/
He limped off the field with a sore leg.
በቆሰለ እግሩ እያነከሰ ከሜዳ ወጣ።

*line* (ላይን)
1. መስመር
He drew a line across the road.
መንገዱ ላይ መስመር አሰመረ።
2. ሰልፍ/አንዱ ከአንዱ ኋላ እየሆኑ መቆም
The soldiers stood in a straight line.
ወታደሮቹ በሰልፍ ቆሙ።

*lion* (ላየን)
አንበሳ
The lion laid watching the zebra.
አንበሳው የሜዳ አህያውን እያየ ጋደም አለ።



*lip* (ሊፕ)
ከንፈር/ጥርሳችንን የምንሸፍንበት የአፋችን ክፍል/
She licked her lips when she saw the chocolate cake.
እሷ የቸኮሌት ኬኩን ስታይ ከንፈሯን ላሰች።


*liquid* (ሊክዊድ)
ፈሳሽ ነገር
That white liquid is milk.
ያ ነጭ ፈሳሽ ወተት ነው።

*list* (ሊስት)
ዝርዝር/የስም/የነገር/
The teacher wrote a list of the boys' names.
መምህሩ የወንዶቹን ልጆች ስም ዝርዝር ፃፉ።

*listen* ('ሊስን)
ማዳመጥ
Did you listen to the teacher in the English class?
በእንግሊዝ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህሩን አዳምጠኸዋል?

*litter* (ሊተ)
ቆሻሻ/ተጠቅመን የምንጥለው ነገር/ውዳቂ
People drop litter in the streets.
ሰዎች በመንገድ ላይ ቆሻሻ ይጥላሉ።

*little* ('ሊትል)
ትንሽ
She has a little doll.
እሷ ትንሽ አሻንጉሊት አላት።



*live* (ላይቭ)
1. አንድ ቦታ መኖር
We live in a house in a big city.
እኛ በትልቁ ከተማ የሚገኝ ቤት ውስጥ እንኖራለን።
2. በሕይወት መኖር
I hope to live for sixty or seventy years.
ስልሳ ወይም ሰባ አመት እንደምኖር ተስፋ አደርጋለሁ።


*lizard* (ሊዘድ)
እንሽላሊት/በተከመረ ድንጋይ ወይም በቤት ጥግ የሚኖር እንስሳ
A lizard lays on the rock in the sun.
እንሽላሊት በፀሀይ ጊዜ አለት ላይ ይተኛል።



*loaf* (ለውፍ)
ሙልሙል ዳቦ
My mother bought six loaves in the bakery.
እናቴ ስድስት ሙልሙል ዳቦ ከዳቦ መጋገሪያ ቤት ገዛች።




*lock* (ሎክ)
1. ቁልፍ/የበር ወይም የሳጥን መቆለፊያ/
The teacher put the lock on the cupboard door.
መምህሩ ቁልፉን በቁምሣጥኑ በር ላይ ገጠመው።



2. እን ድን ነገር ሳጥን ውስጥ ከቶ መቆለፍ
The teacher locked the books in the cupboard.
መምህሩ መፅሀፎቹን ቁምሳጥኑ ውስጥ ቆለፈባቸው።

*log* (ሎግ)
ግንዲላ/የተቆረጠ የዛፍ ግንድ/
He put the logs on the fire.
ግንዲላዎቹን እሳት ውስጥ ጨመራቸው።

*lollipop* (ሎሊፖፕ)
ሎሊፖፕ/የሚመጠጥ ከረሜላ
Children love to lick lollipops.
ህፃናት ሎሊፖፕ መላስ ይወዳሉ።



*long* (ሎን)
1. ቁመቱ ረዥም የሆነ
Monkeys love to climb long trees.
ዝንጀሮዎች ረጃጅም ዛፎችን መውጣት ይወዳሉ።
2. ሩቅ ቦታ ያለ
3. ብዙ ጊዜ የሚወስድ
It's a long way to Diredawa and it takes a long time to arrive there.

ድረጃዋ ሩቅ ነው። እዚያ ለመድረስም ረዥም ጊዜ ይወስዳል።

look (ሉ፡ክ)

1. ወደ አንድ ቦታ መመልከት

Look! There is a bus.

ተመልከት እዚያ አውቶቡስ አለ።

2. መምሰል



My mother looks very tired.

እናቴ በጣም የደከማት ትመስላለች።

(ሉ፡ስ)

የላላ/ያልጠበቀ/በጣም ጠብቆ ያልታሰረ

The dog escaped because the chain was loose.

ሰንሰለቱ ስለላላ ውሻው አመለጠ።

(ሎሪ)

የጭነት መኪና/ለእቃ ማጓጓዣነት የሚያገለግል ትልቅ መኪና/

They put all the boxes in the lorry.

ሁሉንም ሳጥኖች የጭነት መኪናው ላይ ጫኑአቸው።



(ሉ፡ዝ)

አንድን ነገር ሳይታይ ሲያልፍ/ ማለፍ/ መጥፋት ወይም ሳይገኝ ሲቀር።

Did you lose the football match on Saturday?

የቅዳሜው የእግር ኳስ ጨዋታ አመለጠህ?

She always loses her books in school.

እሷ ሁልጊዜ መፅሀፎቿን ትምህርት ቤት ትጥላለች።

(ሎት)

ብዙ

There are a lot of children in the school.

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ብዙ ልጆች አሉ።




***loud*** (ላውድ)
በደንብ የሚሰማ ድምፅ የጎላ
Something that is loud is easy to hear.
የጎላ ድምፅ ያለው ነገር ለመስማት ቀላል ነው።

*love* (ላቭ)
[redacted]መውደድ life
**Fofi loves his mother.**
ፎፊ እናቱን ይወዳል።

*lovely* (ላቭሊ)
ደስ የሚል/ [redacted]
My sister looked lovely in her new dress.
እህቴ በአዲሱ ቀሚሷ በጣም አማረች።

*low* (ለው)
ቁመቱ አጭር የሆነና ዝቅ ያለ
The lorry cannot go under that low bridge.
የጭነት መኪናው በአጭሩ ድልድይ ስር መሄድ አይችልም።



*lunch* (ለንች)
ምሳ /ከቁርስ በኋላ ቀን ላይ የሚበላ ምግብ
She eats her lunch at school.
እሷ ምሳዋን ትምህርት ቤት ትበላለች።

